


ከላሊበላ ሕንፃዎች አንዱ ቤተ ጊዮርጊስ

# ትንሣኤ



«... ዳግመኛ በእናትህ በማርያም ተማጽነናል። ይህችውም አንተን በመውለድ እመቤታችንና የባህር ያችን መመኪያ ናት ። » ( ቅ፡ ዘያዕቆብ ዘሥሩግ ገጽ 180 ቁ. 99 )

ዋጋው ሃምሳ ሣንቲም ቁጥር 41 የካቲት ፲፱፻፸፫ ዓ.ም.

www.ethiopianorthodox.org

‘‘ይህ መጽሔት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ሥርዓትና ዜና ፡ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጐምር እንዲተረ ጐሙ ሊሠራ እንነግ የሚል ስለሆነ ‘‘ትንሣኤ’’ ተብሎ ተሰይሟል ።

አዘጋጅ
ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ
ም/አዘጋጅ ራደ አስረስ ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ሐዋርያዊ ድርጅት
የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ
በወር አንድ ጊዜ
እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 116616
የመልእክት ሣ.ቁ. 3137
አዲስ አበባ

# ማውጫ

ገጽ

አርእስት

ደብዳቤዎች ..................... ፩
ድንግል ማርያምና አማላጅነትዋ ..................... ፪
ቅዱስ ፓትርያርኩ፡ ገዳማተ ላሊበላን ..................... ፬
እምነት ሥነ ምግባርና ፍቅር ..................... ፮
በአርባ ቀን ወደ ቤተ መቅደስ ..................... ፯
ክርስቲያናዊ ጋብቻ ..................... ፲
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
በዓለም የነበራት ታዋቂነት ..................... ፲፩
ምሥጢረ ቁርባን ..................... ፲፪
ይህን ያውቁ ኑሮአል ? ..................... ፲፬
ሢማት በቤተ ክርስቲያን ..................... ፲፮
መልካም ዜና ለአብያተ ክርስቲያናት ..................... ፲፯
ሊቃውንቶቻችን ..................... ፲፰
የመጽሐፍ ቅዱስ ጥያቄዎች ውድድር መልስ ..................... ፳፬

# ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በጥንታዊ ቋንቋዋ ተዘጋጅቶ የታተመ ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስ አላትወይ? ካላት ይህን መጽሐፍ ለመግዛት ስለምፈልግ በየት መጽሐፍ መደብር እንዳገኝ ይጠቁሙኝ ዘንድ በተስፋ እጠባበቃለሁ ።

ምትኩ በጋሻው
አዲስ አበባ

• ምትኩ በጋሻው ስለ ጥያቄዎ እናመሰግንዎታለን እስካሁን ድረስ በግእዝ ቋንቋ በአንድ ጥራዝ የታተመ ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስ የለም ። እርግጥ በግእዝና በአማርኛ በተለያየ ጥራዝ በፎቶ ኮፒ የተባዛ ነበር ። እርሱም አልቆአል። ዛሬ አይገኝም ። ቤተ ክርስቲያናችን ከሁሉ በፊት ስለዚህ ብታስብ መልካም ነበር ።

* * *

ለትንሣኤ አዘጋጅ
አዲስ አበባ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሮች በየሳምንቱ እሑድ ከሰዓት በኋላ እየተከፈቱ ምእመናን የእግዚአብሔርን ቃል እንዲማሩ ለምን አይደረግም?

ተማሪ ሙሉነህ ነገደ
አዲስ አበባ

• ተማሪ ሙሉነህ ነገደ ያቀረብኸው ጥያቄ ተገቢ ነው እንዳልከውም ለጸሎትና ለትምህርት ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመጡ ሰዎች ከተገኙ እንኳን በዕለተ እሁድ በየሳምንቱ በዘወትርም ቢሆን ቤተ ክርስቲያን በሯን ቆልፋ የምትቀመጥበት ምክንያት አይኖራትም በተለይ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ብቻ የተመደቡ ካህናት አሉና ።

የእግዚአብሔርን ቃል ለመማር የሚፈልጉ ምእመናን ካሉ ለዚያው ለሚኖሩበት ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ አሳባቸውን ቢያቀርቡ አስተዳዳሪው በፈለጉበት ሰዓት የቤተ ክርስቲያንን በር ከፍቶ ሊቆያቸውና የእግዚአብሔርንም ቃል እንዲማሩ ሊያደርግ ይችላል ነገር ግን የምእመናን ወደ ቤተ ክርስቲያን መጥቶ ትምህርት መሳተፍና አለመሳተፍ ሳይታወቅ የቤተ ክርስቲያን በር ተከፍቶ መቀመጡ ዋጋ አይኖረውም ።

ስለዚህ ጠያቂው እንደጠየቅኸው በሳምንት አንድ ቀን እሑድ ከሰዓት በኋላ ብቻ ሳይሆን ምእመናን እየተገኙ ትምህርት ለመማር ጸሎት ለመጸለይ ፍላጎት ካላቸው ካህናት የቤተ ክርስቲያንን በር ከፍተው ትምህርት ፈላጊዎች የሆኑትን መምእናን እየተቀበሉ በትምህርተ ወንጌል እንዲያስተናግዱ ምክራቸው በዚህ አጋጣሚ መንፈሳዊ ምክራችን እናስተላልፋለን ። ከዚህም ጋር ምስካየ ሕዙናን መድኃኔ ዓለምንና ማኅደረ ስብሐት ልደታ ማርያምን ቢጐበኙ የርስዎ ሀሳብ ተፈጽሞ ያገኙታል ።

* * *

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

ባለፈው ኅዳር 21 ቀን 1973 ዓ.ም. በቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤ/ክርስቲያን ነበርሁ ። ታቦት በሚወጣበት ሰዓት አካባቢ ‘‘ከተፈቀደላቸው መምህራን በቀር ማንም ግለሰብ ማስተማር አይችልም’’ የሚል ድምፅ ከወደውስጥ በድምፅ ማጉሊያ ይሰማ ነበር ። ለመሆኑ ለማስተማር የተፈቀደላቸውና ያልተፈቀደላቸው እነማን ናቸው?

2. በገጠር ያሉ አብያተ ክርስቲያናት በጥዋፍና በዘቢብ ችግር ቅዳሴ አይቀደስባቸውም ስለዚህ በአዲስ አበባ ያሉ አብያተ ክርስቲያናት ከሞላቸው ጥዋፍና ዘቢብ እያዋጡ ለምን አይረዱአቸውም?

ዲያቆን ብሥራት ፈይሳ
ከደብረ ገሊላ አማኑኤል
አዲስ አበባ

• ቤተ ክርስቲያናችን የስብከተ ወንጌል መምሪያ አላት። መምሪያው ሊሰብኩ የሚችሉትንና የሚገባቸውን መምህራን ይመድባል። ለተመደቡትም መምህራን መታወቂያ እንዲኖራቸው ያደርጋል ። ከዚህ ሌላ ግን የወንጌል መምህር ነው ማለት አይቻልም ። በሌላም መንገድ ለእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን የተመደበ ወንጌላዊ ስለአለ ሌላው ያለ ቦታው ሳይጋበዝ ሄዶ አስተምራለሁ ማለት አግባብ አይደለም ።

ስለ 2ኛው ጥያቄዎ በአዲስ አበባም ሆነ በሌሎች ከተሞች ያሉ አብያተ ክርስቲያናት በገጠር ያሉትን ለመርዳት እጃቸው የሚታጠፍ አይመስለንም ።

ግን ርዳታው በየመንገዱ ሥዕል ዘርግቶ ጥላ አጥልቶ ‘‘እገሌ የተባለው ቤ. ክርስቲያን ተዘግቶአልና ርዱ’’ ለሚለው ለማኝ ሁሉ መሆን የለበትም ። ቤተ ክህነቱ ለገጠር አብያተ ክርስቲያናት የሚያከፋፍል አንድ ማእከል አዘጋጅቶ ከየሀገረ ስብከቶች በኤጲስ ቆጶሳት አማካይነት ሲጻፍለት ቢሰጥ ችግሩ በመልካም ሁኔታ ሊቃለል ይችላል ። ከዚህም ሌላ የአዲስ አበባ አብያተ ክርስቲያናት የገጠር አብያተ ክርስቲያናትን ለመርዳት አንድ ድርጅት ቢያቋቁሙ ይህም ለችግሩ ሌላ መፍትሔ እንደሚሆን እንገምታለን ።

— // —



www.ethiopianorthodox.org

## ርእሰ አንቀጽ

# ድንግል ማርያምና አማላጅነቷ

(አማላጅነት የተጣላ ለማስታረቅ የተቀማ ለማስመለስ የተበደለ ለማስካስ የሚደረግ የማስማማት ተግባ
ር ነው ። እውነተኛ አማላጅ ሰላም በሌለበት ሰላምን ጥላቻ በበዛበት ዕርቅን መሲያየት ባለበት አንድነትን
ይፈጥራል ። ሰውን ከሰው እንዲሁም ሰውን ከእግዚአብሄር ጋር በማሰማማት ሰዎች ከእግዚአብሔር ይቅ
ርታን ያገኙ ዘንድ የደጋግ ሰዎች አማላጅነት አስፈላጊ እንደሆነ ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳል ።
የደጋግ ሰዎች ምልጃ ቁጣን ወደ ትዕግስት መዓትን ወደ ምሕረት ይመልሳል እግዚአብሔርም የደጋግ
ሰዎችን ጸሎትና ምልጃ ይሰማል ። ለወዳጆቹ የሰጠውን ቃል ኪዳን ያስባል ። ስለ ደጋጉ ሰዎች ምልጃና ጸሎት
ለሌሎች ይራራል ፣ ያዝናል ። ዘፍ 18 ፡ 24 - 33 1ኛ ነገ 18 ፣ 36
ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር ለማስታረቅ ከእግዚአብሔር ለሰዎች የኃጢአት ሥርየትን ለማሰጠት የቆ
መች የተፈጠረች እውነተኛ አማላጅ ቅድስት ድንግል ማርያም ናት ። እግዚአብሔር አምላክበኃጢአት
የወደቀውን ሰው ለማዳን የሰጠው ተስፋ እንዲህም የሚል ነበር ” በአንተና በሴቲቱ መካከል ጠላትነትን
አደርጋለሁ ፣ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጥሀል “ዘፍ. 3 ፣ 15
በዚህ ክፍል የሴት ዘር በመባል የተገለጠውና የጠላትን ራስ ይቀጠቅጣል የተባለው ከቅድስት ድንግል
ማርያም ነፍስና ሥጋን ተዋህዶ በመስቀል ተሰቅሎ የሞተውና በእርሱ ሞት የእኛን ሞት አጥፍቶ በድል አድ
ራጊነት የተነሣው መድኃኒታችን ክርስቶስ ነው ። በዚህም የቅድስት ድንግል አማላጅነት ከክርስቶስ ከአዳኝ
ነቱ ሥራ ጋር የተያያዘ መሆኑን እናያለን ፣ እግዚአብሔር ለሰዎች የሰጠው ተስፋ የሚፈጸምበት ዘመን በደ
ረሰ ጊዜ አንድ ልጁን ወደ ዓለም ላከው እርሱም እግዚአብሔር ቃል ከቅድስት ድንግል ማርያም እንበለ ዘ
ርእ ተወለደ ። በሰው ባሕርይ በመወለዱና የሰውን በደል በሰውነቱ በመቀበሉ በግዞት የነበሩትን ነፃ አወ
ጣ ገላ.4፣4 እግዚአብሔር ለሰጠው ተስፋ መፈጸም ድንግል ማርያም ምክንያት ሆነች ። በሥራና በቃል በሥ
ጋና በመንፈስ በደል የሌለባት ንጽሕት ድንግል ሆና ስለተገኘች የአምላክ እናት ለመሆን በቃች ለደኅንነ
ት ምክንያት ሆነች ።
ድንግል ማርያም ለሰዎች ምህረትንና ይቅርታን ታሰጣለች ለኃጥአን ሥርየት ይደረግላቸው ዘንድ
ዘወትር ወደ እግዚአብሔር ትማልዳለች ይህም እውነት እንደሆነ ለመረዳት በቃና ዘገሊላ በሠርግ ቤት በተደ
ረገው የመጀመሪያ ተአምር የእመቤታችን የድንግል ማርያም አማላጅነት እንዳለበት ማስታወስ ይጠቅማል
ነገሩ እንዲህ ነው በገሊላ አውራጃ በቃና ሠርግ ተሠረገ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስና እናቱ ቅድስት ድን
ግል ማርያም ከደቀመዛሙርቱ ጋር ወደ ሠርጉ ቤት ተጠርተው ነበር በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት በሠርጉ
ቤት ተገኙ ። ለሠርግ የተጠሩት ተጋብዘው ሳያበቁ ለሠርጉ የቀረበው ወይን አለቀ ። እመቤታችን ቅድስት
ድንግል ማርያም የወይኑን ማለቅና የባለጉዳዮቹን ችግር ተገነዘበች በእግዚአብሔር ጸጋ ስለተሞላች እግዚአብ
ሔርም ከእርስዋ ጋር ስለሆነ የወይኑን ማለቅና የሰዎቹን ችግር ማንም ሳይነግራት አወቀች በወይኑ ማለቅ ምክን
ያት የደረሰውን ችግር ከባለጉዳዮቹ ወገን አንድ ሰው እንኳን የነገራት አልነበረም ። ግን እመቤታችን ድንግል
ማርያም ስለ ሰዎች ችግር የምታስብ የምትራራና ችግራቸውን ወደ ጌታ አቅርባ ለችግራቸው መፍትሔ የ
ምታሰጥ እውነተኛ አማላጅ በመሆንዋ የሰዎችን ችግር ለጌታ ተናገረች። ባለቤቶቹንም “የሚላችሁን ሁሉ
አድርጉ” በማለት አዘዘች ። ሰዎቹም ለእመቤታችን ታዘዙ እመቤታችንም የአምላክ እናት ናትና ከእርስዋ
ሰው የሆነው አምላክ ምን እንደሚል ታውቅ ነበር ዛሬም ታውቃለች ጌታም የእናቱን ቃል ሳያስተሐቅር
ጋኖች ውሃ እንዲሞሉ አዘዘ። በጋኖች የተሞላውን ውሃ ወደ ወይን ጠጅ በመለወጥ የሰዎቹን ችግር አስወገ
ደ የእመቤታችን አማላጅነት አጸደቀ ።
በመጨረሻም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የአዳኝነት ሥራውን በፈጸመበት በመስቀል ላይ ሳለ
“አንቺ ሆይ እነሆ ልጅሽ” በማለት ዮሐንስን ለመቤታችን የአደራ ልጅ አድርጎ ሰጥቶታል ዮሐ . 19 ፣ 26
በዚህም በዮሐንስ አማካይነት መእመናን ሁሉ ለድንግል ማርያም የአደራ ልጆች ሆነው ተሰጥተዋል ። እርስ



ዋም ለምእመናን ሁሉ ፍቅር የአደራ እናት ሆና ተሰጥታለች ። ስለዚህም ድንግል ማርያም እውነተኛ አማ
ላጃችንና የአደራ እናታችን እንደሆነች እናምናለን ።
በተለያየ ጊዜ የተነሡ የተለያዩ ሊቃውንት በመንፈሳዊ ድርሰታቸው የእመቤታችንን አማላጅነት መስ
ክረዋል ። 1ኛ የሶርያው ሊቅ ቅዱስ ኤፍሬም “አንቲ በአማን ምክሐ ዘመድነ ወሰአሊት ሕይወተ ለነፍሳቲ
ነ በውነት የነገዳችን መመኪያ ለሰዎነታችንም ሕይወትን የምትለምኝልን አንቺ ነሺ”ኤፍሬም 7.9 መስ
ክሮአል ። የእመቤታችን አማላጅነት ከሌሎች ሰዎች አማላጅነት የተለየ ነው አንዳንድ ሰዎች በአማላጅነት
ሲላኩ በተላኩበት አላማ ጸንተው የተበደለውን አስክሰው የተቀማውን አስመልሰው የተጣላውን አስታር
ቀው ከመመለስ ይልቅ ጠብ አባብሰው ይመለሳሉ ። የእመቤታችን ድንግል ማርያም አማላጅነት ግን ሰኃ
ጥአን ሥርየትን ለሰው ልጅ ሁሉ ምሕረትንና ይቅርታን ለማስጠት የታመነ ነው ። “ማርያም ድንግል ንጽ
ሕት ማእመንት ሰአሊተ ምሕረት ለውሉደ ሰብእ ንጽሕት የሆነች ድንግል ማርያም ሰውን ለማማለድ
የታመነች ናት” ኤፍሬም ሶርያዊ
ኢትዮጵያዊው ቅዱስ ያሬድም”.ስምሽን በመጥራት የሰው ልጆችን ልመና ወደ ልዩ ሦስት አብ ወል
ድ መንፈስ ቅዱስ ያሳርጋሉ ። የወገኖችሽንም ኃጢአት ታስተሠርዪ ዘንድ ከአብ ከወልድ ከመንፈስ ቅዱስ
ተፈቅዶልሻል ለሰው ልጆች የዘለዓለም ሕይወት ድልድይ ትሆኚን ዘንድ ። የዓለም ሁሉ መድኃኒት ሆይ ለም
እመናን ወገኖችሽ መድኃኒታቸው ልትባይ ይገባሻል ቅድስት ሆይ ልጅሽ ይቅርታውን ያድለን ዘንድ ለምኚ
ልን ።” በማለት የቅድስት ድንግል ማርያምን አማላጅነት ተናግሮአል ። አንቀጸ ብርሃን የእመቤታችን የድ
ንግል ማርያም አማላጅነት ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ከአዳኝነት ሥራው ጋር የተቀራረበ ነው ።
መድኃኒታችን ክርስቶስ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ ሰዎችን ያዳነው ከእርስዋ በነሣው ባሕርይ ነው።
ምእመናንም እርስዋን ለደኅንነታችን አማላጃችንና መመኪያችን ናት ብለው የሚያምኑት መድኅን
ክርስቶስን በመወለድዋ ነው ። ” ዳግመኛ በእናትህ ማርያም ተማፅነናል ። ይህችውም አንተን በመውለድ
እመቤታችንና የባሕርያችን መመኪያ ናት ። አንተ መታሰቢያሽን ያደረገ ስምሽንም የጠራ የዘለዓለም ደኅን
ነትን ይድናል ብለሃታልና” ቅዳሴ ዘያዕቆብ ዘሥሩግ ገጽ. 180 ፡ ቍ. 99
መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዎችን ለማዳን ወደዚህ ዓለም በመጣ ጊዜ ድንግል ማርያም የአምላክ
መገለጫ ለመሆን በቅታ ተገኝች ። የአምላክ እናት በመሆንዋ መልዕልተ ፍጡራን መትሕተ ፈጣሪ ተባ
ለች ። በሰውና በእግዚአብሔር መካከል መገናኛ ከሃሣር ወደ ክብር ከሞት ወደ ሕይወት መሸጋገሪያ
ድልድይ ከሲኦል ወደ ገነት መውጫ መሰላል ሆነች ። አምላክን የወለደች ድንግልማርያም በእግዚአብ
ሔር አምነው በቃል ኪዳንዋ ጸንተው የሚማጸኑባትን ሁሉ ታማልዳለች ። በሕፀፀ ምግባር ለተሰናከለ የኃ
ጢአት ሥርየትን ታሰጣለች ።
እኛም ከመጽሕፍት ባገኘነውና ከቀደሙን በተማርነው መሠረት አምላክን የወለደች የድንግል ማርያ
ምን አማላጅነት እናምናለን በቃል ኪዳንዋ እንማጸናለን ። ድንግል ማርያም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ
ለተገኘው የሰው ልጆች ደኅንነት መሠረት እንደሆነች እናውቃለን ። “የሕይወት መሠረትናየደህንነት
ጥንት የሆንሽ ማርያም ሆይ ዓለሙን ለማዳን ያማርሽውን መልካሚቱን አንቺን የፈጠረ እግዚአብሔር
ስሙ ይባረክ” ተብሎ ተጽፎአልና ።



www.ethiopianorthodox.org

# ቅዱስ ፓትርያርኩ ገዳማት ላሊበላን ጐበኙ

ብፁዕ ወቅዱስ አቡኑ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክና የቅዱስ ሲኖዶስ ሊቀ መንበር ታኅሣሥ 28እና 29 ቀን 73 ዓ.ም.በወሎ ክፍለ ሀገር በላስታ አውራጃ ተገኝተው በአሠራራቸው በዓለም ተወዳዳሪ የማይገኝላቸውንና ዘጠኝ መቶ ዓመታት ያህል ዕድሜ ያላቸውን ቅዱስ ላሊበላ ያነጻቸውን አሥር አብያተ ክርስቲያን በመጐብኘት የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን በዓለ ልደት አከበሩ ።

ቅዱስነታቸው 1ኛ ብፁዕ አቡነ ኤፍሬምን የአርሲ ሀገረ ስብከት ጳጳስ 2ኛ ብፁዕ ዶክተር አቡነ ገብርኤልን በሐረርጌ ክፍለ ሀገር የሰሜንና የምዕራብ አውራጃዎች ጳጳስ 3ኛ አቡነ ቀሲስ አባ ኃይለ ማርያምን አስከትለው በ28 4 73 ዓ.ም ከጥዋቱ በ2 ሰዓት ከሃምሳ ደቂቃ ላይ (ሹም ሻሐ) ኤሮፕላን ማረፊያ ሲደርሱ 1ኛ ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል የወሎ ሀገረ ስብከት ጳጳስ 2ኛ አቶ መርስዔ ኃዘን አበበ የጠ ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ 3ኛ መምህር ገ እግዚአብሔር ጸጋዬ የፓትርያርኩ ልዩ ጸሐፊ 4ኛ መጋቢ ካህናት ብርሃኑ መኰንን የመንፈሳዊ አገልግሎት መምሪያ ኃላፊ 5ኛ ሊቀ ኅሩያን መርሐ ጽድቅ ገ/ሕይወት የሸዋ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ 6ኛ መልአከ ምሕረት መአዛ ወ ኢየሱስ ም መጋቢ ካህናት ከሌሎች የቤተ ክህነት ሠራተኞች ጋር በመሆን ደማቅ አቀባበል አድርገውላቸዋል ። (ሹም ሻሐ) ኤሮፕላን ማረፊያ የሚገኘው ላሊበላ ካነጻቸው አብያተ ክርስቲያን 12 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ነው ።

(በሹም ሸሐ) ኤሮፕላን ማረፊያ የሚደረገው የአቀበበል ሥነ ሥርዓት እንደ ተፈጸመ ቅዱስነታቸው ብፁዓን ጳጳሳትንና የቤተ ክህነት ባለሥልጣኖችን አስከትለው ቅዱስ ላሊበላ ወደ አነጻቸው ቅዱሳት መካናት አመሩ ።

ቅዱስነታቸው ከተከታዮቻቸው ጋር 12 ኪሎ ሜትር በመኪና ተጉዘው ደብረ ሮሓ ላሊበላ ሲደርሱ ከግራና ከቀኝ መቋት ፣ ከሽድሆና ከዋድላ ደላንታ ልብሰ ተክህኖ ለብሰው ቅዱስነታቸውን ለመቀበል የመጡ ካህናት ከላሊበላ ሊቃውንትና ከአካባቢው ካህናት ጋር ፡ እንዲሁም ገጐጃምና ከጐንደር ከሸዋ ከትግራይና ከወሎ ክፍለ ሃገር አውራጃዎች የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን በዓለ ልደት በላሊበላ ለማክበር የመጡ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ምእመና




ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከብፁዓን ጳጳሳት ጋር በሹም ሸሓ ኤሮፕላን ማረፊያ



ን እጅግ ደማቅና የጋለ አቀባበል አድርገውላቸዋል ።

ቅዱስ ፓትርያርኩ ቅዱስ ላሊበላ በአነፃቸው አብያተ መቅደስ ዓውደ ምሕረት ለአቀባበሉ ሥነ ሥርዓት በተዘጋጀላቸው የክብር ቦታ ላይ ከብፁዓን ጳጳሳት ከሌሎችም የክብር ተከታዮቻቸው ጋር እንደተገኙ ለቅዱስነታቸው የአቀባበል ሥነ ሥርዓት የተዘጋጀው "ይትፌ ነው ለሣህል ኀበ ላሊበላ እምልዑል ቀዋምያን ለነፍሳት እሙንቱ ሊቃናት ተክለ ሃይማኖት ወሳሙኤል" የሚለው ግሥ ተገሥ ለአሥር ደቂቃ ያህል በአስደናቂ ሁኔታ ተዘምሮአል እንዲሁም ከተለያዩ ሊቃውንት የተለያዩ ቅኔያት ለቅዱስነታቸው ተበርከተዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክና የቅዱስ ሲኖዶስ ሊቀ መንበር እጅግ ደማቅና አስደናቂ የሆነውን የአቀባበል ሥነ ሥርዓት ከተመለከቱ በኋላ 1ኛ ቅዱስነታቸውን ለመቀበል ከግራና ቀኝ መቋት ከሽደሆና ዋድላ ድላንታ ለመጡት 2ኛ የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን በዓለ ልደት በዚያ ለማክበርና በቅዱስ ላሊበላ ቃል ኪዳን አማካይነት ሥርየት ኃጢያትን ለማግኘት ከጐጃም ከወሎ ከትግራይ ከጐንደርና ከሸዋ ክፍላተ ሀገር ለመጡትና በብዙ ሺህ ለሚቆጠሩ ካህናትና ምእመናን ሰፋ ያለና እጅግ ጠቃሚ የሆነ መንፈሳዊና አባታዊ ቃለ ምእዳን አሰምተዋል ።

ቅዱስነታቸው ባሰሙት ቃለ ምእዳን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የታሪክ ፣ የቅርጻቅርጽና የሥነ ጽሑፍ ባለጸጋ መሆንዋን አስረድተው የታሪክና የቅርጻቅርጽ መዲና የሆነው የላሊበላ አካባቢ በተፈጥሮ ድርቅ ምክንያት ካህናቱና የአካባቢው ነዋሪዎች መቸገራቸውን በመገንዘብ የካህናቱን ችግር ለማቃለል ካህናቱ እየሠሩ የሚተዳደሩበት የንዋየ ቅድሳት ማዘጋጃ የጉጅ እንዱስትሪ በቅርብ እንደሚቋቋም ተስፋ ሰጥተዋል ።

ከቅዱስ ፓትርያርኩ ቃለ ምእዳን ቀደም ሲል ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል የወሎ ሀገረ ስብከት ጳጳስ የቅዱስ ፓትርያርኩን ጉብኝት አስመልክተው ንግግር አድርገዋል ። ብፁዕነታቸው ባደረጉት ንግግር ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የላስታን አውራጃ ካህናትና ሕዝብ ለመባረክ መምጣቸው ለአውራጃው ሕዝብ መንፈሳዊ መጽናናትን እንደሚሰጠው ገልጠዋል ። ብፁዕነታቸው "ረአይኬ አባግዕየ በጎቼን ጠብቅ" በማለት ለሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የተሰጠውን መመሪያ አስታውሰው ቅዱስነታቸውም ይህንኑ ዘለዓለማዊና አምላካዊ መመሪያ በመከተል በየቦታው እየተዘዋወሩ ምእመናንን በማስተማርና በማ

ወደ ገጽ 8 ዞሮአል



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ቃለ ምዕዳን ሲያሰሙ



www.ethiopianorthodox.org

# “እምነት ሥነ ምግባርና ፍቅር”

የዘመኑ ሳይንስ ተመራማሪዎች በማስረጃ እንዳረጋገጡት እስፈላጊውን የተፈጥሮ ቅመም ወይም ማዕድን በውስጡ ያልያዘ መሬት የዘሩበትን አያበቅልም ፍሬም አይሰጥም ምሳሌ ዘየሐፅፅ ቢሆንም የአገራችን ሊቃውንት እንደሚሉት ምግባር የሌለው ሃይማኖት በዚህ ዓይነት ሊመስልና ሊተረጐምም ይችላል ።

ለብዙዎቻችን እንደሚመስለን ሃይማኖት ያለምግባር የጽድቅ ፍሬን አያፈራም በተስፋ የሚጻስሰውንም ግዳጅ አይፈጽምም ስለዚህ ነው ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ ገና በመጀመሪያው ዘመነ ክርስትና “ ነፍስ የተለየው ሥጋ የሞተ እንደሆነ እንደዚሁ ደግሞ ከምግባር የተለየች ሃይማኖት የሞተች ናት . . . ” በማለት ያስቴማረው ። ያዕ.2. 27 ።

በቅዱሳት መጽሐፍት ተደጋግሞ እንደተነገረው እንደጸሐፊውም የግል አመለካከት ሃይማኖት መሠረት ምግባራት ደግሞ በአንድ መሠረት ላይ ተሰባስበው ና ተያይዘው አንድን ቤት ወደፍጹምነት ሊያደርሱት የሚችሉ ልዩ ልዩ ዓይነት ዕቃዎች /ማቴሪያልስ/ ናቸው ። እነዚያ በአንድ መሠረት ላይ የሚሰበሰቡት ወይም እንደሰንሰለት እርስ በእርሳቸው የሚያዙት ዕቃዎች ቁጥራቸው እጅግ የበዛና በአይነትም በይዘትም የተለያዩ እንደመሆናቸው በሃይማኖት መሠረትነት በክርስቲያናዊ ሕይወት ውስጥ የሚከናወኑት ሥነ ምግባራትም እንደዚሁ ቁጥራቸው የበዛ አይነታቸውም የተለየ ነው ።

እንግዲህ በዚህ አኳኋን ተመሥርቶ የቆመው ቤት ከላይ ደግሞ አንድ ዓቢይ ነገር እንደሚያስፈልገው እናውቃለን ። መዋቅር ወይም ሰብሳቢ ዋልታ እንደዚህም ከሆነ በዚህ ምድራዊ የሕይወታችን ጉዞ ላይ በልዩ ልዩ ጊዜና አጋጣሚ ለሚፈጸሙት ሥነ ምግባራትና ለራሱ ለሃይማኖትም ጭምር ሰብሳቢ ዋልታቸው ወይም የፍጻሜአቸው ጉልላት ፍቅር ብቻ መሆኑ ያለማቋረጥ እየተነገረን ስለሆነ ይህንን እንዳንዘነጋው ያስፈልጋል ። ያለዚህ ፍቅር ምንም ማድረግ አይችልምና ።

ለዚህ ፍቅር ሰፊ አምድ ያልሰጠ የሥነ ጽሑፍ አካል አይገኝም ። ይህን ፍቅር የትምህርቱ መነሻና መድረሻ ወይም የመጀመሪያ ማሳረጊያ የመጽሐፍ ርእስና ዓቢይ አንቀጽ ያላደረገ ሐዋርያ የለም ።

ይህም ያለምክንያት የሆነ አይደለም ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም የመጣበትን አምላካዊ ፈቃድ እስከመስቀል ድረስ አከናውኖ ወደዘለዓለማዊ ክብሩ በሚመለስበት ጊዜ ለነዚያ ከዓለም ለመረጣቸውና ለሚወዳቸው ደቀ መዛሙርቱ እንደዚህ የሚል ጥብቅ አደራ ሰጥቷቸው ስለነበረ ነው ። አደራው ወይም ትእዛዙ አንዱ ብቻ እንዲህ ይላል”. . . . እንደ ወደድኋችሁ እናንተ ደግሞ እርስ በእርሳችሁ ትወደዱ ዘንድ አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ” . . .ይህ ትእዛዝ ይህ ጥብቅ አደራ በክርስቶስ ክርስቲያን ለተባለ ሁሉ እንጂ ለ12 ሐዋርያት ብቻ የተሰጠ የሚመስለው ቢኖር እንዳይሳሳት ይጠንቀቅ ።

ከዚህም ተነሥቶ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወደቆሮንቶስ ምእመናን በጻፈው የመጀመሪያ መልእክቱ ፍቅር ከሁሉ በላይ ፍቅር የሁሉ ነገር መጠቃለያ እንደሆነ እጅግ አስፍቶና አጉልቶ ተናግሮታል እናንብበው

“በሰዎችና በመላእክት ልሳን (ቋንቋ) ብናገር ፍቅር ግን ከሌለኝ

- እንደሚጮህ ናስ ወይም እንደሚንሿሿ ጸናጽል ሆኛለሁ ።

- ትንቢትም ቢኖረኝ ምሥጢርንም ሁሉና ዕ - ቀትን ሁሉ ባውቅ

- ተራሮችንም ሁሉ እስካፈልስ ድረስ ሃይማኖት ቢኖረኝ

- ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ ። ድሆችንም ለመመገብ ያለኝን ሁሉ ባካፍል፣ ሥጋዬንም ለእሳት መቃጠል አሳልፌ ብሰጥ

- ፍቅር ግን ከሌለኝ ምንም አይጠቅመኝም ...” 1ኛ ቆሮ.13፥1 ።

ይህ እንግዲህ የማይለወጠው የጌታ ቃል መሆኑን እናውቃለንና በዘመናችን ከምናሳየው የምእመንነት ተግባር ጋር ስናነፃጽረው ያለጥርጥር ሕሊናችን ልዩ ክብደት ይሰማዋል ። ምናልባትም ከዚህ ኃይለ ቃል ላይ ሕሊናችን ፈጥኖ እንዲሸሽ ካላደረግነው በቀር እጅግ አድርጐ የሚያስደነግጥና ውስጣዊ መንፈስን በረቂቅ ኃይል የሚመታ ሆኖ እናገኘዋለን ። አባባሉ ትርጉም አያሻውም ምክንያቱም አያጠያይቅም

ሐዋርያው እንደሚለው ይህን ሁሉ አድርጐ ያለፍቅር መጽደቅ ካልተቻለ ብዙዎቻችንም /ማለትም/ ሥነ ምግባር የጐደለው ፍቅር ያልዳሠሠው ባዶ እምነት ብቻ ይዘን ራሳችንን የምናታልል ሁሉ ያለ ጥርጥር «ዘምቶ ተወረሰ» መሆናችን የሚያጠያይቅ ነውና ቢሆንም በጌታ ቃል እየታገዝን ነቅተንና ተግተን እንማራለን እናስተምራለን እንዲያም እያልን የጽድቅን አክሊል እስክንቀዳጅ ደጅ እንጠናለን እንጂ ተስፋ አንቆርጥም ። ተስፋ መቁረጥ የመጨረሻው ሽረትም ውድቀትም ስለሆነና ክርስቶሳውያንም ስለሆንን ተስፋ አንቆርጥም ።

ገብረ ጊዮርጊስ አጋዝ

---



# በአርባ ቀን ወደ ቤተ መቅደስ

በዘመነ ኦሪት ሲሠራባቸው ከነበሩት ሥርዓቶች አንዱ ወንድ ልጅ በተወለደ በ40 ቀኑ ሴት ልጅ በተወለደች በ80 ቀኗ በወላጆቻቸው አማካይነት ወደ ቤተ መቅደስ መግባታቸው ነበር ። ሕፃናቱ በወላጆቻቸው አማካይነት ወደ ቤተ መቅደስ ከተወሰዱ በኋላ በዚያው ቤተ መቅደስ የሚፈጸምላቸው ሥርዓት ነበር ። ሥርዓቱም በኦሪት ዘሌዋውያን 12 ተጽፎ ይገኛል።ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሕግ ባለቤት ሲሆን እኔ ሁሉን ለማድረግ አይሳነኝምና ሰው በሠራው ሕግና ሥርዓት አልሄድም ። ራሴ ሕግ አውጥቼ በራሴ ሕግ መመራት እለብኝ አላለም ክርስቶስ ከኃጢአት በስተቀር የዕብራውያንን ሥርዓትና ሕግ እየፈጸመ አድጓል ።

በኦሪት ሥርዓት መሠረት በተወለደ በ8 ቀን ወደ ቤተ ግዝረት ተወስዶ ሥርዓተ ግዝረት ሲፈጸምለት በ40 ቀንም ዘመዶቹ ወደ ቤተ መቅደስ ይዘውት ገብተዋል ። በዚያም በኦሪቱ ሕግ መሠረት የርግብና የዋኖስ ጫጭት ሠውታለታል በዚያን ጊዜ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን መወለድ በተስፋ ሲጠባበቅ ለብዙ ዓመታት የኖረ ስምዖን የሚባል ሰው ሕፃኑን ኢየሱስን በክንዱ አቀፈው ወዲያው ምክብሴት(ከእርጅና)ታደሰና እንደ ዋሊያ ዘለለ እንዲሁም መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጆችን ከሞተ ነፍስ ነፃ ለማውጣት ወደፊት ስለሚቀበለው ጸዋትወ መከራ ሰፋ አድርጎ ተናግሯል ።

የአረጋዊውን ስምዖን ታሪክ በአጭሩ እንመለከተዋለን በዚያ ዘመን በጥሊሞስ የሚባል አንድ ገናና ንጉሥ ነበር ከገናነቱም የተነሣ ይህንን ዓለም እንደ ሰም አቅልጦ እንደ ገል ቀጥቅጦ ይገዛ ነበር ይላል ብዙ ቋንቋዎችንም ያውቅ እንደነበር ይነገራል ከዕለታት አንድ ቀን የቅርብ አማካሪዎቹን ሰበሰበና ሁሉን አድርጊያለሁ የቀረኝ ነገር ምን አለ? አላቸው ከአማካሪዎቹ መካከል አንደኛው ተነሣና አዎን ብዙ ነገሮችን አድርገሃል ነገር ግን 46 ብሉያት መጻሕፍት ቀርተውሃል ከእነርሱ ብዙ ጥበብ ብዙ ምሳሌ ይገኛል እነርሱን ከዕብራይስጥ ቋንቋ ወደ ድርዕ እንዲተረጉሙ ብታደርግ መልካም ነው አለው።

በጥሊሞስበዚያ ዘመን በእስራኤላውያን ላይ ሠልጥኖባቸው ስለነበር ጸሐፍቱንና መጻሕፍቱን ላኩልኝ ብሎ ላከባቸው እነርሱም 46ቱን ብሉያትና ሰባ ሁለቱን ጸሐፍት ላኩለት ከጸሐፍቱ ሁለቱ ከመንገድ ቀርተዋል ሰባው ግን ደርሰውለታል እርሱም ለሰባው ሊቃናት የሚላላካቸው አንዳንድ ተላላኪ እያደረገ አንድ ድንኳን ለሁለት ሰጣቸው ታናናሹን መጻሕፍት አንድ ላንድ ታላላቁን ለሁለት መደበና የዕብራይስጡን ቋንቋ ወደ ጽርዕ (ግሪክ) መልሱ አላቸው በዚያን ጊዜ መጽሐፈ ኢሳያስ በዕጣ ለስምዖን ደረሰውና ሲጽፍ ድንግል በድንግልና ጸንሳ ትወልዳለች ከሚለው አንቀጽ ደረሰ ይህንን ቃል ብጽፍ ስንኳንስ የአሕዛብ ንጉሥየእስራኤልንጉሥ ሊቀበለኝ ይችላል? አለና ድንግልን ፋቆ ወለት ብሎ ጻፈ ወዲያው እንቅልፍ መጣበትና ተኝቶ ቢነቃ መልአኩ ወለትን ፋቆ ድንግልን ጽፎአገኘው ሁለት ጊዜያት ድንግልን ፋቆ ወለት እያለ ከጻፈ በኋላ ለሦስተኛ ጊዜ ድንግልን ፋቆ ወለትን እጽፋለሁ ሲል ይህንን የተጠራጠርከውን ነገር ሳታየው አትሞትም ብሎ ነግሮታል ።

ስምዖን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ እጅግ ሸምግሎ ስለነበር ዓይኑ ፈዝዞ ጉልበቱ ደንግዞ የተነገረውን ቃል በተስፋ ይጠባበቅ ነበር ክርስቶስ በኦሪቱ ልማድ ሊፈጸምለት ወደ ቤተ መቅደስ በተወሰደ ጊዜ ሕፃኑን በክንዱ ሲታቀፍ ድካሙ ሁሉ አልተሰማውም ድካሙና እርጅናው ሁሉ ተወገደለትና ተነሥቶ እንደ ዋሊያ ዘለለ ፣ጌታችን ኢየሱስ ክርስቸስም ትወድ እንደሆነ በዚህ ላስቀምጥህ ብሎት ነበር

ነገር ግን በተስፋ ሲጠብቀው የነበረው ቃል ስለተፈጸመለት በዚህ ዓለም እንደገና ብዙ ዘመን ለመኖር አልፈለገም። ከዚህ ዓለም በፍቅርና በሰላም እንዲያሰናብተው«ጌታ ሆይ አሁን እንደ ቃልህ ባርያህን በሰላም ታሰናብተዋለህ። ዓይኖቼ በሰዎች ሁሉ ፊት ያዘጋጀኸውን ማዳንህን ዓይተዋልና ይህም ለአሕዛብ ሁሉን የሚገልጥ ብርሃንህን ለሕዝብም ለእስራኤል ክብር ነው።» ሲል ስንብትን ከፈጣሪው ጠይቋል ፣ ሉቃስ 2.25 - 32

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የኦሪቱን ሕግ መሠረት በማድረግ በተወለደ በ40 ቀን ወደ ቤተ መቅደስ ተወስዶ መሥዋዕት እንደተሠዋለትና አረጋዊው ስምዖንም በክንዱ እንደታቀፈው አሁንም እኛ ወንድ ልጅ በተወለደ በ40 ቀን ወደ ቤተ ክርስቲያን ወስደን አስጠምቀን ምሥጢረ ቁርባንን እንዲቀበል አድርገን ወደቤቱ እንዲመለስ እናደርጋለን

ሁለተኛ ደግሞ ሕፃናቱ ወደ ቤተ ክርስቲያን ገብተው በመጠመቅ ከሥላሴ ልጅነትን እንዲቀበሉ የምናደርገው የአዳምንና የሔዋንን ወደ ምድረ ገነት መግባት አብነት በማድረግ ነው።

ስለዚህ በመጽሐፈ ኩፋሌ የተጻፈው ቃል «በተፈጠረበት ምድር ለአዳም 40 ቀን ከተፈጸመለት በኋላ ይገዛትም ይጠብቃትም ዘንድ ወደ ገነት አስገባው ይልና ከዚያም በማያያዝ ሔዋን ሚስቱንም በሰማንያ ቀን ወደ ገነት አስገባናት ይላል መጽ.ኩፋ.4.9. ይኸው መጽሐፍበተጨማሪም ከዚህ በኋላ ኤዶም ወደ ምትባል ወደ ገነት ገባች ስለዚህ ነገር ወንድ ልጅ ብትወልድ ቀድሞ አዳም ሰባት ቀን ቆይቶ እንደተፈጠረበት ሰባት ቀን በአራስነትዋ ትቆይ ዘንድ 33 ቀንም ንጽሕ በሚሻደምዋ ትቆይ ዘንድ ልጅ ለምትወልድ ሴት በጽላት ሰማይ ሥርዓት ተጻፈ ንዋየ ቅዱሳትንም አትንካ ለወ



www.ethiopianorthodox.org

ንድ ልጅ የታዘዘውን ይህንን ቀን እስክ ትፈጽም ድረስ ወደ ቤተ መቅደስም እን ዳትገባ ሥርዓት ተጻፈ ይላል።

በሌላ በኩል የሥነ ፍጥረት ሊቃውን ት በሰው ተፈጥሮ በኩል ባደረጉተ ጥናት ላይ የሰው ልጅ ሲጸነስ ተስዕሎት መልክ ዕ የሚፈጸምለት ከአባቱ አብራክ ተከ ፍሎ ከእናቱ ማኅፀን በተጣለ በ40 ቀኑ ነው ይላሉ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ወንድ ልጅ በተወለደ በ40 ቀን ወደ ቤተ ክርስቲያን ወስዳ የምታ ጠምቀው ይህንን የመሰለውን ሥርዓት መነሻ በመደረግ ነው።

ስለዚህ ወንድ ልጅ በተወለደ በ40 ቀን ሴት ልጅ በተወለደች በ80 ቀኗ ወደ ቤተ ክርስቲያን ተወስደው እንዲጠመቁና የክርስትና አባትና እናትም እንዲኖራቸው የሚደረገው ከላይ እንደ ተጠቀሰው ከጥንት ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው መሠረት ነው።

ቄስ ልሳነ ወርቅ በዛብህ

## ቅዱስ ፓትርያርኩ

ከገጽ ፭ የዞረ

ጽናናት ቅዱሳት መካናትን በመጐብኘት የሚያደርጉት ሐዋርያዊ ተልእኮ ለዕውነተኛ ሐዋርያነታቸው ምልክት ኖትንና ተከታዮቻቸውን ፣ በላስታ አውራጃ ካህናት ፣ ምእመናንና በራሳቸውም ሥም እንኳን ደኅና መጣችሁ በማለት ሰፋ ያለ መግለጫ ሰጥተዋል ።

መምህር በሰጡት መግለጫ እንደ ዛሬው የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ ሳይ ታሰብ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይ መዋዕለ ሕፃናት በማሠራት ያደረጉትን ከፍተኛ ተጋድሎ አስታውሰው ይህም ቅዱስነታቸው ለኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝብ አሳቢና ተቆርቋሪ ዕውነተኛ መንፈሳዊ አባት መሆናቸውን እንደሚያስረዳ ገልጠዋል ። መምህር ገለጣቸውን በማራዘም የላስታ አውራጃ የተፈጥሮና





ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ላሊበላ ሲገቡ በተደረ ገው የአቀባበል ሥነ ሥርዓት ላይ ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል የወሎ ሀገረ ስብከት ጳጳስ ንግግር ሲያደርጉ

መሆኑን አስረድተዋል ።

ከብፁዕ አቡነ ሳሙኤል ንግግር በፊ ት መምህር ብርሃነ ሥላሴ መንበሩ የላ ስታ አውራጃ ቤተ ክህነት ሥራ አስኪ ያጅ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማ ኖት ያልተማሩ የሚማሩበትን ትምህርት ቤት ፣ ድሆች በሽተኞች የሚታከሙበትን ክሊኒክ ፣ አሳዳጊ የሌላቸው ሕፃናት በእንክብካቤ አድገው የነገዋን ኢትዮጵያ ለመረከብ የሚሉበትን ሰው ሠራሽ ችግር የተፈራረቀበት በመ ሆኑ ከታሪካውያን ቦታዎች በቀር ሌላ ምንም አይነት ተስፋ የሌለው መሆኑን አሳስበው በአውራጃው የሚገኙትም ካ ህናት እነዚህኑ ታሪካውያን ቦታዎች



ከመጠበቅና አብያተ ክርስቲያናቱን ከማገልገል በቀር ምንም አይነት መተዳደሪያ እንደሌላቸው አስረድተዋል ።

መምህር ብርሃነ ሥላሴ መንበሩ በላ ስታ አውራጃ ስለሚገኙት አብያተ ክር ስቲያናት ሲገልጡ በአውራጃው ውስጥ 550 ያህል አብያተ ክርስቲያናት እንደ ሚገኙ ገልጠው፣ከእነዚህም መካከል ዙሪያ ገኖ በሚታይበት ወቅት እነዚህ ን አስመስሎ ማነፅ ይቅርና በጨው ባሩድና በዕድሜ ብዛት ምክንያት የሚሰነ ጠቁትን ለማደስእጅግአድካሚና አስቸጋሪ መሆኑ ሲታይ ከብዙ መቶ አመታት በፊት በዚህ አውራጃ ከፍተኛ ምርምርና ዕውቀት እንደነበረ መገንዘብ የሚቻል መሆኑን ገልጠዋል ።

የቀደሙት አበው በቅርስነታቸው የ ሀናት በኩል ያለውን ይዘት ሲያስረዱ በአውራጃ ውስጥ በሚገኙት አምስት መቶ ሃምሳ አብያተ ክርስቲያናት ሃያ ሺህ 20.000 ያህል ካህናት እንደሚገኙ ተናግረዋል ።

መምህር ስለታሪካውያን ቦታዎች የወደፊት ሁኔታ ሲገልጡ የላሊበላ ፣ የይምርሃ ፣ የነአኩቶለአብ ፣ የገነተ ማር ያም ፣ የብልባላ ጊዮርጊስ ፣ የአቡነ አ





መምህር ብርሃነ ሥላሴ መንበሩ ገለጣ ሲያደርጉ

ሰማንያው ያህል ታሪካውያን አብያተ ክርስቲያናት ሲሆኑ አሰራራቸው እጅግ የሚያስደንቅና የሚያኮራ የሀገር ቅርስና አለኝታ ሲሆን ታይቶ የማይጠገብ መሆኑን አብራርተዋል ።

አብያተ ክርስቲያናቱ የታነፁት እን ደዛሬው ቴክኖሎጂ እደ-ጥበብ ሰማይ ሳይደርስና ጠፈርን ሳይመረምር ሲ ሆን ዛሬ ስልጣኔ ተስፋፍቶና በዓለም ሚያኮሩና መንፈሳዊ በረከትን የሚያ ድሉ እነዚህን አብያተ ክርስቲያናት ሲያንፁ ለመንፈሳዊ ጥቅም ብቻ ሳይ ሆን ለሥጋዊ ተድላ ደስታም ጭምር ታስቦባቸው መሆኑን ዛሬ ከምንመለከተው ጢስ አልባ እንዱስትሪነታቸው መረዳት እንደሚቻል መምህር በገለጣቸው አስረድተዋል ።

መምህር ብርሃነ ሥላሴ መንበሩ በካ ሮን እና የመሳሰሉት ታሪካውያን ሕንፃ ዎች አስቸኳይ ጥናት ካልተደረገላቸው ወደፊት እንዲህ ነበር እያሉ ከማውራት በስተቀር መተካት ወይንም ማስተካከል የማይቻል መሆኑን አሳስበው በዚ ህም ረገድ ጠቅላይ ቤተ ክህነት የታ ሪክ ተጠያቂነት ያለበት መሆኑን አስረ

ወደ ገጽ ፲፱ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

## ወጣቶች በቤተ ክርስቲያን



በወጣትነህ ወራት ፈጣሪህን አስብ (መክ. 12-1)

አዘጋጅ ኢሳይያስ ወንድማገኘሁ

# ክርስቲያናዊ ጋብቻ

ጋብቻ በፆታ የሚለያዩ ሁለት ግለሰቦችን አንድ የሚያደርግ ታላቅ የፍቅር ሰንሰለት ነው ስለዚህም «ሰው እናትና አባቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር አንድ ይሆናል» ተብሎ ተጽፏል። ይህን ቃል የተናገረው በሥነ ፍጥረት ጊዜ«ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት» ብሎ ሴትና ወንድን በፆታ ለይቶ በፈቃድና በፍቅር እንዲዋሐዱ ያደረገ እግዚአብሔር ስለሆነ ቃሉ የታመነ ነው።

እንደተባለውም ወንዶች ሚስቶቻቸውን ሴቶችም ባሎቻቸውን የሚከተሉትና የጋብቻን ቀምበር የሚሸከሙት ለጊዜያዊ ፍቅር ብቻ ሳይሆን ዘላቂ የሆነ ኑሮዋቸውን በጋራ መሥርተው በአንድ ልብና አሳብ ፀንተው እየተረዳዱ ለመኖርና መልካም ዘርን ለመተካት ነው።

የጋብቻ ዋና ዓላማ 1ኛ ተረዳድቶ ለመኖር 2ኛ.መልካም ዘርን ለመተካትና ፈቃደ ሥጋንም በሕጋዊ መንገድ ለመፈጸም ሲሆን አንዳንድ ጊዜ ከሕግ ውጭ በሆነ ግንኙነት ጋብቻቸውን የሚመሠርቱ ሊኖሩ ይችላሉ እንደነዚህ ያሉትም ባልና ሚስት ተብለው በስም ብቻ ይጠሩ እንጂ የጋብቻቸውን መሠረታዊ ሁኔታ ስንመረምር በድቡሽት ላይ እንደተመሠረተ ሕንፃ ነውና በዘላቂነት ተስፋ የሚጣልበት ስላልሆነ አስተማማኝ አይደለም ። ለምን ? ቢባል በሕጋዊ መንገድ ተጋብተው በቃል ኪዳንና በክርስቲያናዊ ሥነ ሥርዓት የተጋቡ ባለመሆናቸው እሱ ወይም እሷ በትዳራቸው ላይ እምነት ስለማይኖራቸው ነው።ምክንያቱም ጋብቻቸው «ባጣ ቆይኝ» ስለሆነ በላዬ ላይ አጭቶ ይሆን?ምናልባት ከአንዱ ጋር ተዋውላ በድንገት ትከዳኝ ይሆን? » የሚሉ ጥያቄዎች በሴቷ ወይም በወንዱ አእምሮ መጉላላቱ ስለማይቀር ነው።ይህ ዓይነቱ ትዳር የጊዜ ማሳለፊያ እንጂ ዘላቂና አስተማማኝ ባለመሆኑ የሴቷንም ሆነ የወንዱን ሞራል የሚገድልና ሥጋዊውንም ሆነ መንፈሳዊ ዓላማቸውን የሚያቃውስ ነው።

ለመሆኑ ሕገወጥ ለሆነ ግብቻ መንሥኤው ምንድነው? የዚህ ዋና መንሥኤው ዘማዊነት ሲሆን ባሕልና ልማድን ተከትለው የሚመጡ ብዙ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ። ለምሳሌ ያህልም አንዳንዶቹን መጥቀስ ይቻላል ።

ሀ፡ በዘማዊነት 1ኛ በሠራተኛ መልክ ተቀጥረው በቤት ሠራተኝነት ከገቡ በኋላ ሲውሉ ሲያድሩ ፈቃደ ሥጋቸውን ለመፈጸም ሲሉ በሚያደርጉት ቅጽበታዊ ግንኙነት በሚመጣው ዲቃላ ምክንያት ወይም በግብረ ሥጋ ግንኙነት ከመለማመዳቸው የተነሣ እስከ ጊዜው ድረስ ይሁን /ትሁን በሚል ስሜት ብቻ ያለ ዓላማቸውና ያለ ፍላጎታቸው የልብ ሳይሆን የአፍ ጋብቻ ፈጽመው ባልና ሚስት እየተባባሉ የሚኖሩ አሉ ።

2ኛ ሴቶች በዝሙት አዳሪነት ወይም በልዩ ልዩ ዓይነት ሥራ እየተዳደሩ ብቻቸውን በሚኖሩበት ወቅት አንዳንድ ወንዶች በወዶ ገባነት /ገሌ ገብተው በሴቷ ቤት በሚቀመጡበት ጊዜ ባልና ሚስት እየተባሉ ይጠራሉ በአመቻቸውና ፍቅራቸው ባለቀ ጊዜ ግን ወጥተው ይሄዳሉ።

ለ. በልማድ 1ኛ እንደ ሚስት በሰማንያ እንደገረድ በደምወዝ በሚል የውል ሰነድ ተፈራርመው የሚቀመጡ ነበሩ። ይህም ሴቷ የሀብቱ ተካፋይ ሆና ገንዘቡን እንዳትቆጣጠረውና ከቤቱ በምትሄድበትም ጊዜ የሀብቱ ተካፋይ ስለማትሆን በፈቀደ ጊዜ ለማብረር እንዲያመቸው ነው።

2ኛ. በጠለፋ ሴቷ ልጅ ፈቃድዋ ሳይሆንና በጋብቻው ሳታምንበት በመንገድ ተጠልፋ ወደ አንዱ ቤት እንድትገባ የሚደረግበት ጊዜ አለ ይህ የሴቶችን መብት የሚነካ ከመሆኑም በላይ በዚህ ሁኔታ የተያዘው ትዳር ዘላቂነት የለውም

3. አንድ ወንድ ለሁለት ወይም ከዚያ በላይ ቁጥር ላላቸው ሴቶች ባል የመሆን ጉዳይ ነው ይህም የሴቶችን መብት የሚነካ ነው። ክርስቲያናዊ ጋብቻ አንድ ወንድ በአንዲት ሴት አንዲትም ሴት በአንድ ተወስነው እንዲኖሩ የሚያዝና ሕጋዊ የሆነ ሲሆን አንድ ሰው ብዙ ሴቶችን አግብቶ በመኖር ላይ እያለ ክርስቲያን ነኝ ቢል የክርስትናን ሕግ አፍርሷልና የሚደገፍ አይደለም በዚያው ም ላይ በኑሮ በኩል ችግርን የሚፈጥር ነው።

ወደ ገጽ ፲፪ ዞርአል



# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በዓለም የነበራት ታዋቂነት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊት እንደመሆንዋ መጠን በዓለም ዘንድ ታዋቂነትና ግንኙነት እንደነበራት የታሪክን መዛግብት ብንመለከት ብዙ መረጃ ልናገኝ እንችላለን በዘመኑ ብሉይ ያለውንና የነበረውን የቤተ መቅደሱን ታሪክ ወደ ኋላ ትተን በአራተኛው ምዕት ዓመት መጀመሪያ ላይ ቤተ ክርስቲያኗ የነበራትን ታዋቂነት እንመረምራለን ።

ከላይ በተጠቀሰው ዘመን ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያውን ታዋቂነት ያገኘችው የግሪክ ተወላጅ በሆነው በአቡነ ሰላማ አማካኝነት ነው። ይህም መንፈሳዊ አባት ቤተ ክርስቲያንዋን በግሪክ ከምትገኘው ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን በግብፅም ሆነ በምሥራቅ ከሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ጋር አስተዋውቀዋታል ። ምንም እንኳን የክርስትና ትምህርት በጃንደረባውና በቅዱስ ማቴዎስ ቢሰበክም በዚያ ዘመን የነበሩት የአይሁድ ምኩራቦች ወደ ቤተ ክርስቲያን ስላልተለወጡ ቤተ ክርስቲያን ታዋቂነት አልነበራትም ማለት ነው ።

አቡነ ሰላማ ጳጳስ ከሆን ወዲህ ግን ምኩራቦች ወደ ቤተ ክርስቲያንነት ስለተለወጡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በእምነት ፡ በሥነ ሥርዓት ፡ በባሕል በዓለም ዘንድ ታዋቂነትን ጀመረች ይህንንም ጉልህ የሚያደርገው በእስክንድርያ ያለው የግሪክ ኦርቶዶክስ ፓትርያርክ የግሪክ ተወላጅ የሆነውን የአክሱም ሊቀ ጳጳስ በማለት እየሾመ ወደ ኢትዮጵያ እስካሁን በመላኩ ነው ቀጥሎም በአምስተኛው ምዕት ዓመት የቢዛንታይን መንግሥት ከሚያስተዳድራቸው ልዩ ልዩ ሀገሮች የተውጣጡ ዘጠኙ ቅዱሳን በእምነትዋ በሥነ ሥርዓትዋ ወደ ታወቀችው ወደ ኢትዮጵያ መጡ ትምህርታቸውንም ሆነ አገልግሎታቸውን ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን አበረከቱ እነርሱም ያስተማሩት ትምህርትና የሰጡት አገልግሎት ቤተ ክርስቲያንዋን ወደ ታላቅ የመንፈሳዊ እድገት ደረጃ ስላደረሳት በቅርብም ሆነ በሩቅ ምስራቅ ዘንድ ከፍ ያለ ታዋቂነትንና መልካም ግንኙነትን ሊያስገኝላት ችሎአል ።

ከዚህም የተነሣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የቢዛንታይን መንግሥት በሚገዛቸው አገሮች ሁሉ ታዋቂነትንና ግንኙነትን እያገኘች ሄደች ይህም በመሆኑ ጉዳዮችን እንደፈጸመላት ይነገራል ከነዚህም መካከል ጥቂቶቹን እንጥቀስ ምንም እንኳን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በኢየሩሳሌም ካለው ቅዱስ ቦታ ይዞታዋ ቀደም ያለ ቢሆንም እንዲስፋፋና በውስጡም ያሉት መነኮሳት እንዲበረታቱ ልዩ ልዩ እርዳታ ያደርግ እንደነበረ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያብራራል በጠቅላላው በቢዛንታይን ዘመነ መንግሥት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በሥነ ጽሁፍ በመንፈሳውያን ሊቃውንት በባሕል የታወቀች ስትሆን ለአገልግሎት ንዋየተ ቅድሳት እንደወላንሳ ምንጣፍ፣ ፃህል፣ ጽዋእ መስቀል ጽንሐሕ፣ ካባ፣ ላንቃ ካባ ቀሚስ እነዚህ ሁሉ በአዶሊስ በኩል ይመጡላት እንደነበር ይህ ታሪክ በተጨማሪ ይናገራል ይህም ድርጊት በስድስተኛውና በሰባተኛው ምዕት ዓመታት የቤተ ክርስቲያንዋን የኑሮ ሁኔታ አብራቶ ያሳያል (በዚህ ዘመን ብሩህ የሆነውን መንፈሳዊ እርምጃዎችን ንና በአለም ዘንድ የነበራትን ታዋቂነትና ፣ ግንኙነት ያስፋፋችበት ወቅት በመሆኑ በዘመኑ የነበሩት የታሪክ ፀሐፊዎች የቤተ ክህስቲያንዋን ዕድገት ለማሳወቅ እንደጣሩ ያሳያል ይህንንም እሙን የሚያደርገው « በአምስተኛውና በሶስተኛው ክፍለ ዘመን የተዋህዶ እምነት በአርመን አገር ውስጥ ያገኘው ድል አርመናውያንን ፡ ሶሪያውያንን ፡ ግብጾችን ፡ ጆርጃውያንን አክሱማውያንን በግንኙነት አንድ አድርጎአቸዋል እነዚህም ስለ አገሮቻቸው ሁኔታ ስለ ባሕላቸው ስለ ሃይማኖታቸው መስፋፋት እንዲተባበሩ አድርጎአቸዋል » ሲል ኮቪሽቻኖብ ጽፎአል ይህም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ከነዚህ አገሮች ጋር ሰፋ ያለ ታዋቂነት ብቻ ሳይሆን በመንፈሳዊ ተግባርም በኩል ተካፋይ እንደነበረች ያብራራልናል ቀስተ ደመና የተባለውም መጽሔት በሚያዝያ ወር 1980ዓ.ም. እ.አ በወጣው እትሙ በገጽ 12 ላይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ከአርመን ቤተ ክርስቲያን ጋር የነበራትን ታዋቂነት ሲያብራራ « የአርማንያ ከተማ ሊቀ ጳጳስ በ17ተኛው ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያን እንደጎበኙና ጉዞውም ሁለት አመት እንደወሰደበት ያብራራል ቀጥሎም ለ14 ወራት ያህል ከንጉሥ ዮሐንስ ጋራ በጎንደር ቤተ መንግሥት እንደቆየና ፡ ፍርድ ቤቱን የቤተ ክርስቲያንን አስተዳደር እንደተመለከተ ይናገራል ።

በተጨማሪም በኑጋዶው አሻኔስ ጽሑፎች ውስጥ ያሉትን ነገሮች ሲያብራራ የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ባሕሎችና ጠባዮች የሕዝቡን የእለት ኑሮ እንዲሁ የኢትዮጵያ ኦርቶድክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሁኔታ » ይገልፃል። እንዲህ ያለውም አኳኋን የሚያብራራልን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ከአ



www.ethiopianorthodox.org

ርማንያ ቤተ ክርስቲያን ጋር ብቻ ሳይሆ ን በዚያን ዘመን ከነበሩት ምሁራን ጋር ምን ያህል ተዋቂነትና ግንኙነት እንዳ ላት ነው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ከራሺያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክ ርስቲያን ጋር የነበራት ታዋቂነት እንዲ ህ ነበር 1891 ዓ.ም. በራሺያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሲኖዶስ ዉሳኔው መሰ ረት አባ ቲሸንና አባ ጎርጎርዮስ የተባሉ ት ሁለት መነኮሳት ከኢትዮጵያ ኦርቶዶ ክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖ ዶስ የተላኩት መነኮሳት ኢትዮጵያ ለመ ድረስ አልቻሉም ።

ቀጥሎም 1894 ዓ.ም የራሺያ ኦርቶዶ ክስ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ቆሞ ስ ኤፍሬም (የሕክምና ሊቅ ዶክተር) የሊሲብንና ሊዮንቲዬሸን ወደ ኢትዮጵ ያ ላከ እነዚህም መልእክተኞች ኢትዮ ጵያ ገቡ የያዙትንም ገፀ በረከት ለአፄ ምኒልክ ለሊቀ ጳጳሱ ለአቡነ ማቴዎስ አቀረቡ ለአንድ አመትም ያህል ተቀ መጡ ቆሞስ ኤፍሬምም «ጉዞ በሀገረ አ በሻ» በሚል ርእስ የአገሪቱንና የቤተክ ርስቲያንዋን ታሪክ የሚገልጽ አንድ መጽሐፍ ጻፈ ይህም በኢትዮጵያና በራ ሺያ ቤተ ክርስቲያን መካከል ያለውን መንፈሳዊ ግንኙነት ሊያሳድገው ችሉ አል ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ከራሺያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክ ርስቲያን ጋር የቅርብ ግንኙነት ለማድ ግና ጉብኝት ለመለዋወጥ በ1895 ዓ.ም አራት ልዑካን ተሳኩ ሦስቱ በመንግሥ ት በኩል ሲሆኑ ቤተ ክርስቲያንዋን ወ ክለው የተላኩት የሐረር ሊቀ ካህናት የ ነበሩት ቆሞስ አባ ገብረ እግዚአብሔር ናቸው። ከዚያም እንደደረሱ በክብር ተቀ ብሎዋቸው ኡስፔስኪይ በተሰኘው ካቴ ድራል ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበት አባ ገብ ረ እግዚአብሔር ንግግር አድርገው ሕዝ ቡን ባረኩ። ጉብኝታቸውንም በመቀጠ ል በፒተር ቡርግ አሌክሳንደር ኔብስኪ ይ የተባለውን ታላቅ ገዳም ጎበኙ ።

የፒተር ቡርግ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ፓላዩ ስ ከሕዝቡ ጋር ትልቅ አቀባበል አደረ ጉላቸው አባ ገብረእግዚአብሔር ና አብ ረዋቸው የሔዱት መልእክተኞች ስለ ሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት ግንኙነት ንግግር እንደተለዋወጡ ቆሞስ ኤፍሬም የጻፈው መጽሐፍ ያብራራል።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሁለቱ አብያተ ክ ርስቲያናት ግንኙነታቸውን እንደቀጠሉ ናቸው ይኸውም የራሺያ ኦርቶዶክስ ቤ ተ ክርስቲያን የኢትዮጵያን ሊቃውንት በየጊዜው እያሰለጠነች ለኢትዮጵያ ኦር ቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በማበ ርከት ላይ ትገኛለች በ1970 ዓ.ም በግ ንቦት ወር ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የራሺያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክር ስቲያንን ጎብኝተዋል የኢትዮጵያ ምሁ ራንንም በልዩ ልዩ የሞያ ዘርፍ የምታ ሠለጥናቸውን የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ቤተ ክርስቲያን በ1972 ዓ.ም. በሚያ ዚያ ወር ጎብኝተዋል ይህም ጉብኝት በነ ዚህ አብያተ ክርስቲያናት መካከል የነ በረውን ግንኙነት ፍሬአማ አድርጎታል።

እንግዲህ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋ ህዶ ቤተ ክርስቲያን በዓለም አብያተ ክ ርስቲያናት ዘንድ ታዋቂነትና ጥንታዊ ነት ስላላት የክብር ደረጃዋ የተጠበቀ ነው (ሆኖም ክርስቶስ « የፊተኞች የኋ ኞች ይሆናሉ የኋለኞችም የፊተኞች ይ ሆናሉ» ሲል አስተምሮአል በዚህ መሰ ረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤ ተ ክርስቲያንም ጥንታዊና ታዋቂ ፤ ፊተ ተኛ ብትሆንም በኋላዋ የተነሱት እየቀ ደሙዋት ሲሄዱ እስዋ ግን ወደ ኋላ በመ ቅረትዋ ሁልጊዜ ተረጂና ተቀባይ ሆና ትታያለች ሊቃውንት የሉዋትም እንዳ ትባል ሊቃውንት ሞልተዋታል መጻሕ ፍትም አሉዋት ችግሩ ተባብሮ አለ መስራት ስለሆነ ቤተ ክርስቲያንዋን በ ሥራ ለማስቀደም ተባብረን እንሥራ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ

## ክርስቲያናዊ ጋብቻ

ከገጽ ፲ የዞረ

4. የመንደር ጋብቻ፡- ይህ ዓይነቱ ጋ ብቻ በሀገራችን በብዛት የሚታይና በጣ ምም የተለመደ ነው ሆኖም የሰፈር ሽማ ግሌ ሰብስበው ከነዚያው መካከል የውል አባት አበጅተው በልማዳዊ አሠራር እ ንደተጋቡ ሁሉ ሲፋቱም እንደዚሁ እነ ዚያኑ ሽማግሌዎች ሰብስበው ፊርማቸ ውን በመቅደድ ብቻ መፋታት ስለሚች ሉ እንደዚህ ያለው የጋብቻ አመሠራረ ት ከዘላቂነቱ ይልቅ በቶሎ መፍረሱ ስለሚያመዝን አስተማማኝ ነው ለማለ ት አያስደፍርም ።

እንግዲህ ከላይ የጠቀስናቸውና በዚ ህ ጽሑፍም ያልተጠቀሙት ሌሎች የጋ ብቻ ሥርዓቶች በዝሙትና በልማዳዊ አሠራር ላይ የተመሠረቱ ስለሆኑ ለክር ስቲያኖች የሚስማሙና በቤተ ክርስቲ ያን መጻሕፍት የተፈቀዱ አይደሉም። ለክርስቲያኖች የተፈቀደው የጋብቻ ሥ ነ ሥርዓት ሁለቱ ወጣቶች ለአካለ መ ጠን ከደረሱ በኋላ ተስማሚያቸውን ፈ ልገው ጊዜያዊ ስሜትን ለማርካት ብቻ ሳይሆን ለእውነተኛ ው ትዳር ተስማሚ ዎች መሆናቸውን አምነውና ተማምነ ው እስከመጨረሻዋ የሕይወት ዘመና ቸው አብረው በትዳር ለመኖር ወስነው በሕጋዊ መንገድ ከተጫጩ በኋላ ዘመ ዶቻቸውን አስፈቅደው በተክሊልና በ ቁርባን የሚፈጸሙት ሥርዓተ ጋብቻ ዘላቂና አስተማማኝ ሊሆን ይችላል።

ማንኛውም ክርስቲያን ወጣት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በተክሊልና በቁርባን ሥርዓት ጋብቻውን በሚፈጽምበት ጊዜ ሴቷም ሆነች ወንዱ የሚገቡት ቃል ኪ ዳን ስላለ ያንን ቃል ኪዳን በሚገቡበት ወቅት በቄሱ አማካይነት የሚሰጣቸው ምክርና የሚቀርብላቸው መሐላ እሷም ሆነች እሱ ከጋብቻ ውጭ እንዳያመነዝሩ ና ከተጋቡ በኋላ መፋታት ከባድ ኃጢ አት መሆኑን በይበልጥ የሚያስገነዝብ ስለሆነ በመካከላቸው አንዳንድ ጊዜያዊ

ወደ ገጽ ፲፮ ዞሮአል



## የሃይማኖት ዐምድ

«ዓለሞች ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተዘጋጁ ፤ ስለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን» (ዕብ. ፲፩፡፫) ።

## ምሥጢረ ቁርባን

(የቁጥር 40 ተከታይ)

ሥጋዊ ምግብ በየዕለቱ የሚያስፈል ገንን ያህል ቅዱስ ቁርባንም መንፈሳዊ ምግብ ስንቀ ነፍስ በመሆኑ ምን ጊዜ ም አስፈላጊ መሆኑን ክርስቲያን ሁሉ ሊያውቀው ይገባል።

ክርስቶስ ይህን ታላቅ ምሥጢር በም ግብና በመጠጥ መልክ ያቀረበበት ም ክኒያት « አብሮ የበላና የጠጣ ቅዱስ ዮ ሐንስ /ወይም ዘመን / እንኳ አይሽረው ም እንዲሉ ሰውንና እግዚአብሔርን አን ድ በማድረግ የሚያዋሕድ የፍጹም አን ድነት መታወቂያ ማኅተም በመሆኑነው ይህን ቅዱስ ሥጋና ደም ቁርባን የሚ ቀበሉ አማኞች የዘላለም ሕይወትን ስለ ሚወርሱ የሞት ሞት ወይም ዳግም ሞት እየተባለ የሚጠራው ሞተ ነፍስ አያገኛ ቸውም ራእይ 21.8 ለደዌ ሥጋም ፈ ውስን ይሰጣል።

ስለዚህ ነው ያራሲዎች እንኳ በመሰ ንቆ ዜማ ሲዘምሩ « ዳኑ አሉ ሁሉም የታ መሙ በሥጋውና በደሙ»ይሉ የነበር በሌላም በኩል ብዙዎች አማኞች ስለቅዱስ ሥጋ ወደሙ ክብር የተነገሩት ን አንዳንድ ቃላት ያለትርጉም በማጤን ከኃጢአት ሳይነጹ መቁረብ «ፍዳ ያመ ጣብናል ብለው በመፍራት የወጣትነ ትና የጎልማሳነት ዘመናቸው ተፈጽሞ የእርጅናቸው ጊዜ እስኪደርስ መጠባበ ቅ ይወዳሉ ነገር ግን በመኖር እንዣር መሞት አለና ዕርጅና በቀጠሮ አይመጣ ም ስለዚህ ለማስታወስም በሌላው ጎብ ር ቅኔ ከተነገረው ድርሰት

« የተሰቀለውን ሥጋውን ሳልበላ
ይደርሳል ሰዓቱ ሳስብ ሌላ
- ከሥጋው ሳልበላ ተጸይፈ ደሙን
ማን ይችለው ይሆን የላይ ቤት እ ራቡን?
ሚመጠን ሳይባል የመጣሁ ቅድሚ
ሥጋውና ደሙ አለቀብኝ በኔ»

ወዘተ የሚል ይገኝበታል።

ተጠንቅቀውና ተዘጋጅተው የሚኖሩ ሥጋው ደሙ የተሠራው ለኃጢአት ማ ስተሠሪያ መሆኑን የተገነዘቡት ዕውነ ተኞች አማኞች ግን ምን ጊዜም ለመቁ ረብ ዝግጁዎች መሆናቸውን ለማመል ከት ከተነገሩትም «ቢላዋዬንስዬ እጠባበ ቃለሁ

ሥጋ አምላክ ቢሰጥኝ እበላበታለሁ»

እንጀራ አልፈልግም ምን ያደርግል ኛል ቆርጬ እሄዳለሁ ሥጋው ይበቃኛል የተሰኙትን የቅኔ ድርሰቶች ማስታወ ስ ይጠቅማል። እነዚህም የቅኔ ድርሰቶች ከቅዱስ መጽሐፍ ቃል ጋር የሚተባበር መልእክት አላቸው ለማስረጃ «ሥራች ሁና ድካማችሁ ሁሉ ለሚጠፋ ምግብ ብቻ አይሁን ይልቅስ የዘለዓለም ሕይ ወት ሆኖ ለሚኖረው የሰው ልጅ ተብሎ የሚጠራው ክርስቶስ ለሚሰጣችሁ መ ብል ሥሩ እርሱን እግዚአብሔር አብ አ ትሞታልና»የሐ.6.27.የሕይወት እንጀ ራ እኔ ነኝ ወደኔ የሚመጣ ከቶ አይራብ ም በኔ የሚያምን ሁልጊዜ አይጠማም» ሲል ራሱ ክርስቶስ የተናገረውን ቃለ ወ ንጌል ልናስታውስ ይገባል ።

በመሠረቱ ከክርስቶስ ጋር ፍጹም አን ድነት ኅብረት የሚኖረው በዚሁ በቅ ዱስ ቁርባን አማካይነት ነው። ስለዚህ ም ነው ወንጌላዊው ሐዋርያ ዮሐንስ በ መጀመሪያ መልእክቱ1.7.9«እርሱ በብ ርሃን እንዳለ እኛም በብርሃን ብንመለ ስ ለእያንዳንዳችን ኅብረት ይኖረናል የ ልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢ አት ሁሉ ያነፃልናል ። ኃጢአት የለብን ም ። ብንል ራሳችንን ማታለል ይሆንብ ናል ዕውነትም በእኛ ውስጥየለም።ኃጢ አታችንን ብንናዘዝ ይቅር ሊለንና ከዓመፃ ሁሉ ሊያነጻን እርሱ የታመነ እውነተኛ ነው » ሲል የጻፈ እንግዲያውስ « ከሰው ስሕተትከብረት ዝገት አይታጣም እን ዲሉ ከዕውነተኞች አማኞች የሚፈለግ ታላቁ ቁም ነገር በደለኛነትን ተረድቶ መናዘዝ እንጂ «ሰማይ እንኳ በፊቱ ንፁ ሕ ሊሆን አይችልም የሚለውን ንጹሕባ ሕርይ አምላክ ለማታለል ጻድቅ መስሎ መታየቱ ግብዝነት ነው። ራሳችንንማ ንጹሓን ጻድቃን ብንሆን ኖሮ የክርስቶ ስ ወደ ዚህ ዓለም መምጣትና መወለድ ሥጋ መልበሱ ባላስፈለገም ነበር። ኃ ጢአት በዓለም ባይኖር ወይም የሰው ዘር ሁሉ ከኃጢአት ባርነት ፈጽሞ ነጻ የሚሆንበት ቅጽበት ቢኖር የኃጢአ ት መደምሰሻ የሆነው የቅዱስ ሥጋ ወደሙ ሥርዓት ባላስፈለገም ነበር ። ነገር ግን የሰው ዘር ሁሉ እስካለ ድረ ስ ኃጢአትም መኖሩ የማይካድ በመ ሆኑ ይህ የኃጢአት ሁሉ ማስተሥረያ የሆነው ቅዱስ ቁርባን መሠረቱ እየ ታወቀ አማኞች በየአብያተ ክርስቲ ያናቱ እየተገኙ አስቀድሰውና ተሳል መው ብቻ መመለሳቸው ታላቅ ምሳ በ ተዘጋጀበት አዳራሽ ገብቶ ሳይመገቡ በባዶ ሆድ ወጥቶ እንደመሄድ ያስቆጥር ባቸዋል።

ምናልባት በቅዳሴው ማዕከል ካህኑ «ሳይገባቸው ከዚህ ሥጋና ደም ለመቀ በል ቢቀርቡ ለሚመጣባቸው ፍዳ መተ ላለፍ የለብኝም » የሚለውን ቃል በመስ ማት እንደሚሆን ይህ ቃል የሚነገረው በተለይ ቅዱስ ሥጋ ወደሙ አማናዊ የ ክርስቶስ ሥጋና ደም መሆኑን ሳያምኑ በመጠራጠር ለመቀበል የሚቀርቡትን መናፍቃን ለመገሠጽ ክብሩንም ለመግ ለጥ እንጂ ለኃጢአት ማስተመረያ ይሆን ዘንድ አትቀበሉ ማለት አይደለም።

እንዲያውም መድኃኒት የሚያስፈል ገው ለሕሙማን እንጂ ለጤነኞች ባለመ ሆኑ ቅዱስ ቁርባንም የተሠራው ለኃጢ አት መደምሰሻ ለመንግሠተ ሰማያት መውረሻ ባጠቃላይ ለሕይወት መታደሻ መሆኑን ምዕመናን ሁሉ ሊያስተውሉት ይገባል።

ቆ .መክብብ አጥናው



www.ethiopianorthodox.org

# ይህን ያውቁ ኖረዋል ?

እጅጉ ረታ

ካለፈው የቀጠለ

ዝናም ሕይወት ላላቸው ነገሮች ሁሉ እጅግ በጣም አስፈላጊ መሆኑ አያከራክርም ። ዝናም ባይኖር ኖሮ ምድራችን ዕፀዋትን አዝርዕትንና አትክልትን ልታበቅል አትችልም ነበር። ዝናም ባይኖር ኖሮ ፣ ባጠቃላይ መሬት ሕይወት ያለው ማናቸውም ፍጡር ሊኖርባት የማትችል ውበትና ልምላሜ የማይታይባት ፍጹም ደረቅ፣ ምድረ በዳ እንደምትሆን አይጠረጠርም ። በመሠረቱ ዝናም ከወደላይ የሚወርድ ውሀ መሆኑን እናውቃለን ። ውሐም በተፈጥሮ ሕግ በተወሰነለት ድግግሞሽ መሠረት ፣ በሦስት ሁኔታዎች ( ኩነታት የሚገለጥ መሆኑ እንግዳ ነገር አይደለም ውሐ ሲረጋ፣ በረዶ ሆኖ እንደ ድንጋይ መጠጠሩ እንዲሁም ቀዝቅዞ ከመጠጠሩና ተፍለቅልቆ ከመትነኑ በፊት በፈሳሽነት መልኩ መታየቱ መገኘቱ ከፈላና ከተፍለቀለቀ በኋላ ደግሞ ወደ ተንነት መለወጡ የተፈጥሮ ሕግ ሂደት መሆኑ ዛሬ በውል ተረጋግጧል ።

ከምድር ገጽ ሩቡ 1 4 ያህል የብስ ወይም መሬት ሲሆን ሶስት እጅ 3 4 በባሕር የተሸፈነ ነው ። እንግዲህ ዝናም በምንልበት ጊዜ ይህን ምድርን ተንሰራፍቶ በስፋት ከያዛት ውቅያኖስ በሙቀት ኃይል ወደ ተንኖት ተለውጦ ወደ ላይ በመውጣት ከረጋ በኋላ እንደገና ወደ ምድር ተመልሶ በመውረድ የሚንጠባጠበውን ውሐ ዝናብ መግለጻችን እንጂ ሌላ ነገር አለመሆኑ ዛሬ በዘመናዊ የሳይንስ ጥናትና ምርምር ተደርሶበታል። ይሁን እንጂ ስለዚህ ጉዳይ መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረው ነገር አለ?

“ እርሱ የውሐውን ነጠብጣብ ወደ ላይ ይስባል ። ዝናብም ከጉም ይንጠባጠባል ። ደመናት ያዘንባሉ ኢዮብ 36፣ 27-29 ዝቅ ይልናም በ37ኛው ምዕራፍ ቁጥር 11 ላይ “...የውሐውንም ሙላት በደመና ላይ ይጭናል...” ይላል ። በአማርኛው መ ቅ ደመና የሚለውን ቃል እንግሊዝኛው ትነት ቬፐር ነው የሚለው እብራይስጡም እንደዚሁ ነው የሚለው እሉ ። ዳዊትም፡-“ ...ከምድር ዳር ደመናትን ያወጣል ፣ በዝናም ጊዜም መብረቅን አደረገ ። ነፋሳትንም ከመዛግብቱ ያወጣል ። ... መዝ. 135 ፣ 5-7 ። ይላል ። እኒህ ከዚህ በላይ የተመለከቱት ጥቅሶች ከዛሬ 2500 ዓመት በፊት የተነገሩ ናቸው ። በዚያን ዘመን የነበሩ ሰዎች ራሳቸው ኢዮብና ዳዊትም ጭምር ዛሬ በጥናት እኛ ስለዝናብ የምናውቀውን ሁሉ ያውቁ ነበር ብሎ ለማሰብ በእውነቱ አስቸጋሪ ይሆናል ።

ሳያቋርጥ በየዕለቱ በሙቀት ኃይል ከውቅያኖስ ባሕር የሚነሳው ትነት ኢቫፖሬሽን ወደላይ ከወጣ በኋላ ከፍ ብሎ ከሚገኘው ቀዝቃዛ አየር ሲደርስ ይኸው ቀዝቃዛ አየ ስለሚጫነው ወይም እንደ ልብስ ጠቅሎ ስለሚይዘው ምሳ. 40 ፣ 4 ይረጋና ደመና ይሆናል ። ደመናውም ከውቂያኖስ ወደ ላይ በወጣበት አቅጣጫ ረግቶ የሚቀር ከሆነ ተመልሶ እዚያው እውቂያኖስ ውስጥ ስለሚጥል ስለሚዘንብ ለመሬት የሚሰጣት አንዳችም ጥቅም አይኖርም ።

በመሠረቱ ማናቸውም ፍጥረት ያለ ምክንያት ያለ ዓላማ እንዲያው ባጋጣሚ የተፈጠረ የተገኘ አይደለም። ቀድሞውኑ ሲፈጠር ግቡን ለመምታት የየራሱ ተልእኮ ያለው በመሆኑ፣ ይህን የመፈጸም ግዴታ አለበት ። የዝናብም ከዚህ የተለየ አይደለም ። በዘፈቀደ ከውቅያኖስ ተነስቶ በዘፈቀደ ወደ ላይ ወጥቶ በዘፈቀደ ተመልሶ እውቅያኖስ ሊገባ አይችልም ማለት እራሱን በራሱ አያዝም ። በተወሰነለት ሥርዓት መሠረት ኢዮ.28 ፣ 6 በትንቢተ ኢሳይያስ ምዕ. 55 ፣ 10 በመጽሐፈ ኢዮብ ምዕ.38፣25-27እንደተጻፈው የመፈጸም ግዴታ አለበት። ስለዚህም የነፋስ ኃይል ደመናውን እየነዳ ወስዶ ዝናብ እንዲጥል ያደርገዋል ። ይህም “ነፋሳቱን ለተልዕኮ ከመዛግብቱ ያወጣቸዋል”የሚለው ቃል ትክክል መሆኑ በዘመናዊ የሳይንስ ጥናት ተረጋግጧል ።

ደመናው በነፋስ ኃይል እየተነዳ ወደ አንድ ከፍተኛ ቦታ ወይም ትልቅ ዛፍ አጠገብ ሲደርስ በደመናው ውስጥ ባሉት ኤሌክትሮንስ መብዛት ወይም ማነስ ምክንያት በሚደረገው የመሳሳብ ኃይል መብረቅ የሰማይ ብልጭታ የነጎድጓድ ጉርምርምታ ይፈጠራል ። ይህም የሳይንስ ምሑራን አባ·ል ፣ “በዝናብ ጊዜ መብረቅን አደረገ” የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ያጸናል ። በሌላም ቦታ “ፈሳሾች ሁሉ ወደ ባሕር ይሄዳሉ ዳሩ ግን አይሞላም ። ፈሳሾች ወደ ሚሄዱበት ሥፍራ እንደገና ወደዚያ ይመለሳሉ” ይላል ። መክ. 1፣7 ።

ባጠቃላይ በዓለም ላይ የሚገኙ ወንዞች ሁሉ ወደ ውቅያኖስ የሚፈሱ ሲሆን ውቅያኖሶች ግን እንደማይሞሉ ከጥንት ጀምሮ የታወቀ ነው ። ትርጉሙንት ወይም ምንነቱ ያልታወቀው ግን እንደገና ወደዚያ ይመለሳሉ የሚለው ሐረግ ነው ። ይሁን እንጂ ጸሐፊው የዛሬ 2800 ዓመት ገደማ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተቃኝቶ የተናገረውን ቃል ዘመናዊ ሳይንስ ምክንያቱን እንደሚከተለው አድርጎ አቅርቦታል ።

የፈለገውን ያህል ውኃ ወደ ውቅያኖስ ቢፈስም የውቅያኖስ ውሐ በዚያው መጠን ያለማቋረጥ እየተነነ በመነሳት ወደ መጣበት የሚመለስ እንደገናም በመዝነብ ከወንዞች ጋር ተቀላቅሎ ወደ ውቅያኖሶች የሚፈስ ሂደቱም ያለማቋረጥ በተደጋጋሚ የሚከናወን ነው ይላል።

ወደ ገጽ ፲፮ ዞሯል



# ልማት በቤተ ክርስቲያን

አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን መስዋእት አድርጎ ለመሠረታትና በደሙ ላነጻት ቤተ ክርስቲያን የሃይማኖት አባቶችና የምእመናን መሪዎች እንዲኖሩዋት የወደደና የፈቀደ መሪዎችዋ በየዕለቱ በምእመናን መካከል እየተገኙ እንዲቆጣጠሩ የደከመውን እንዲያጽናኑ የታመመውን በጸሎት እንዲያድኑ በክህደት የተሰነካከለውንና ልቡ የተሰበረውንም በሃይማኖት እንዲጠግኑ በልዩ ልዩ ስብከት ተወናብዶ የባዘነውንም በትክክለኛ ቃለ ወንጌል እንዲመልሱና ከምእመናንም ተለይቶ የጠፋውን እንዲፈልጉ እንጂ እንዲሁ ለታይታ አይደለም ።

አዎ መልካም እረኛ የበጎቹን ብዛት ከማወቁም በላይ የያንዳንዳቸውንም ስም ጠንቅቆ ያውቃል በዚህም መሠረት ሁሉንም በየስማቸው ሲጠራቸው ጠባቂያቸው መሆኑን ለይተው ስለሚያውቁት እሱን ተከትለው ወደሄደበት ቦታ ይሄዳሉ ።

ግን የበጎቹን ብዛትና ስማቸውን ለይቶ የማያውቅ ከሆነ መንደኛ እንጂ እውነተኛ የበጎች ጠባቂ ነው ለማለት አያስደፍርም በጎቹም ቢሆኑ ምንም እንኳ መላልሶ ቢጠራቸው ጠባቂ ያቸው አለመሆኑን ስለሚያውቁ ፈጽመው ሊከተሉትና ዘወር ብለው ሊያዩት አይችሉም እውነተኛ ጠባቂ አይደለምና ።

እንግዲያውስ በዚህ አንጻር ምእመናንን በቀና መንገድ ለመምራት ቤተ ክርስቲያንንም ለመጠበቅ በኃላፊነት የተረከቧት የቤት ክርስቲያን አባቶች በሀገረ ስብከታቸው ያሉትን ምእመናን የያንዳንዳቸውን ስም ማወቅ ያስፈልጋቸዋል የያንዳንዳቸውንም ስም ማወቅ ባይቻል በሀገረ ስብከቱ ውስጥ ያሉት ምእመናን ምን ያህል ብዛት እንዳለባቸው ማወቅ ግዴታቸው ነው ።

ይህንንም መሠረት በማድረግ በከፋ ሀገረ ስብከት ምን ያህል ምእመናንና አብያተ ክርስቲያናት እንደዚሁም አብያተ ክርስቲያናቱ በምን እንደሚተዳደሩ ለመረዳት የከፋ ሀገረ ስብከት ጳጳስና የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ ብፁዕ አቡነ ኤልሳዕን አነጋግረናቸው ነበር ።

ትንሣኤ በከፋ ሀገረ ስብከት የምእመናንና የአብያተ ክርስቲያናቱ ብዛት ምን ያህል ይሆናል?

ብፁዕ አቡነ ኤልሳዕ በከፋ ሀገረ ስብከት ውስጥ 280 አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ እነዚህም ጥንታውያንና አዳዲስ የተሠሩ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው።

ትንሣኤ ጥንታውያንና አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናት ማለትዎ እንዴት ነው ከለውጡ ወዲህ ወይም ብፁዕነትዎ ወደዚህ ሀገረ ስብከት ከሄዱ ወዲህ ምን ያህል አብያተ ክርስቲያናት የተሠሩ ቢኖሩ ነው?

መልስ አዎ አዳዲስ ብዬ የጨመርኩት ከለውጡ ወዲህ በዚህ በ6 ዓመት ውስጥ ከ 30-40 ድረስ ብዛት ያላቸው አብያተ ክርስቲያናት ተሠርተዋል ።

ትንሣኤ አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናት እንዲሠሩ የተፈለገው ለምን ነበር? አማንያን ስለተጨመሩ ነው ወይስ ተጨማሪ ቤተ ክርስቲያን ስላስፈለገ ነው?

አቡነ ኤልሳዕ አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናት እንዲታነፁ የተፈለገውና እኛም እንዲሠሩ የፈቀድነው ብዙ ምክንያቶች አሉ ይኸውም ከ 1966 ዓ.ም. ማለትም ከለውጡ በፊት የነበረው አስተዳደር ሰፊው መሬት በተወሰኑ ባላባቶችና በጉልተኞች እጅ ስለነበረና ባላባቶችና ጉልተኞችም መሬቱን አስፋፍተው ከመያዛቸው የተነሣ በብዙኃኑ ክርስቲያኖች ከባድ ችግር ይደርስባቸው ነበር ችግሩም ምእመናኑ በፈቀዱት ቦታና በአካባቢያቸው ቤተ ክርስቲያን ሠርተው ጸሎት ሊያደርሱ የተወለደውንም ልጅ በቤተ ክርስቲያኑ ሥነ ሥርዓት ወ:ድ በ40 ቀኑ ሴት ልጅም በ80 ቀንዋ ክርስትና ለማስነሣት እንዲሁም ከመካከላቸው አንድ ሰው ሲሞት በአቅራቢያቸው እንዲቀብሩ መብት አልነበራቸውም

ምእመናኑ ክርስቲያኖች እንደመሆናቸው መጠን መንፈሳዊ አገልግሎትንና አምልኮተ እግዚአብሔርን የሚፈጽሙበት ቤተ ጸሎት በአቅራቢያቸውና በአካባቢያቸው መሥራት ሲገባቸው መብታቸው ተገፎ ኢሰብአዊ ድርጊት ሲፈጽምባቸው ኑሯል ። ግን ከየካቲት 25 ቀን 1967 ዓ.ም. ወዲህ የጉልተኛውን ሥርዓት ደምስሶና የገጠር መሬት ለብዙኃኑ ሕዝብ የሚያደርገው ዓዋጅ ስለወጣና መሬት ለአራሹ ተብሎ ከመታወጁም በላይምዕመኑም እንደቀድሞው ወደቃልቻ ና ወደ ልዩ ልዩ አምልኮተ ባዕድ መሄዱን ትቶ - ተስፋውና አለኝታው እግዚአብሔር መሆኑን ተገንዝቦ ወደ ቤተ ክርስቲያን በመመለሱ ሲሆን በሌላም በኩል በአንድ በአላባት መሬት ላይ ከ700-800 ምዕመናን በሚገባ ተደራጅተው የጸሎት ቤት እንዲሠራላቸው ስለጠየቁን ለዘመጽአ ኀቢየ ኢየሰድዮ አፍአ” ወደ እኔ የመጣውን አልለቀውም ወደ ውጭም እንዲሄድ አላሰናብተውም በሚለው አምላካዊ ቃል መሠረትና የእነሱንም መብት ለመጠበቅ ስንል በአቅራቢያቸውና በአካባቢያቸው ቤተ ክርስቲያን ሠርተው እንዲጠቀሙና ችግራቸውን እንዲያስወግዱ ፈቅደንላቸዋል ።

ይኸውም ተገቢ ሆኖ ስላገኘነው ነው እኛ የእነሱን ችግር ተመልክተን በአካባቢያቸው ቤተ ክርስቲያን እንዲሠሩ ማሳሰብና ማስተባበር ሲገባን እነሱ ራሳቸው አስበው ቤተ ክርስቲያን ሠርተን እንድንጠቀም ይፈቀድልን ብለው ሲጠይቁን የማንፈቅድበት ምክንያት ስለማይኖር ነው ።

ትንሣኤ ምእመናኑ ከቃልቻና ከልዩ ልዩ አምልኮ ባዕድ ተላቅቆ በቤተ ክርስቲያን ሥር መጠለሉና በብዛት እየጨመሩ መሄዳቸው ይመሰገናል ነገር ግን አ



www.ethiopianorthodox.org

ብያተ ክርስቲያናቱ ከቀድሞ ይልቅ በብዛት መታነጻቸውና ምእመናንም እየበዙ እንደመሄዳቸው መጠን እነሱን የሚያገለግሉና እየተዘዋወሩም የሚያስተምሩ ብቁ መምህራን ይገኛሉ ወይ ? መምህራኑስ በምን ይተዳደራሉ ? ብፁዕ አቡነ ኤልሳዕ መምህራን በብዛት ባይኖሩም በዚሁ ሀገረ ስብከት የሚገኙት ካህናት በቅዳሴም ሆነ በማኅሌት በጠቅላላ በቤተ ክርስቲያን የሚፈጸመው መንፈሳዊ አገልግሎት እየተወናፈሉ ስለሚያገለግሉ በቤተ ክርስቲያን ችግር የለም ስለ መተዳደሪያቸውም በከተማ ያሉትና በሰበካ ጉባዔ የተጠናከሩ ካህናት ሕፃናትን በማስተማር እንዲሁም በገጠር ያሉት ካህናት የገበሬ ማኅበራት በየቤተ ክርስቲያኑ አካባቢ ያለውን የእርሻንና የአትክልትን ቦታ በመስጠት

ከሀገረ ስብከቱ ጋር ስለተባበሩና ቤተ ክርስቲያንም የራሳቸው መሆንዋን ስለተገነዘቡ ካህናቱን በዚህ ዓይነት ያስተዳድሩአቸዋል ።

ትንሣኤ የከፋ ሀገረ ስብከት ብዙ ኢአማንያን እንደነበሩት የታወቀ ነው ብፁዕነትዎ ሀገረ ስብከቱን ከተረከቡት ወዲህስ ወደ ክርስትና ሃይማኖት የተመለሱት ስንት ይሆናሉ ?

አቡነ ኤልሳዕ ከላይ እንደገለጽኩት የቃልቻና የአምልኮ ባዕድ እየጠፋ በመሄዱ በየዓመቱ ከአንድ መቶ በላይ በክርስቶስ ስም እያመኑ ጿጋ ክርስትናን ይቀበላሉ በየዕለቱ ወደዚች ሃይማኖት የሚመጡት ኢአማንያን ከዕለት ወደ ዕለት እየጨመሩ ናቸው ።

አዎ በጎች ሲረቡና በጥቂት ጊዜ ሊበዙ የሚችሉት ትጉና ንቁ እረኛ/ጠባቂ ሲኖራቸው ነው ።ልምላሜና ጥሩ ውሃ ባለበት ቦታ እያሠማራ የሚጠብቃቸው ሲሆን ነው ።

እንደዚሁም ሁሉ ምእመናኑ ሊበዙ ቤተ ክርስቲያንም ልትስፋፋ የምትችለው ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል ሰውነቱን ለማስተማር መስዋዕት የሚያደርግ የሃይማኖት አባት ሲገኝ ነው ።

ከነፈ እርግብ ማርቆስ

## ክርስቲያናዊ . . . . . .

ከገጽ ፲፪ የዞረ

ችግር ቢፈጠርም በትእግሥትና ርስበርሳቸው በመመካከር ችግሩን አስወግደው በሰላም እንዲኖሩ ይረዳቸዋል። ከዚህም ጋር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በካህኑ አማካይነት የገቡት ቃል ኪዳንና የፈጸሙት ሥርዓተ መሐላ ሕሊናቸውን እየወቀሰ ጨዋዎች እንዲሆኑ ስለሚያደርጋቸው በዚሁ አንጻር በመካከላቸው ፍጹም መተማመን ሊኖር ይችላል። መተማመኑ ካለ ደግሞ ጠብና ንትርክ ፈጽሞ ይወገድና «አንተ ትብስ አንቺ ትብሽ»እየተባባሉ በሰላምና በፍቅር ስለሚኖሩ ለራሳቸው ሰላማዊ የሆነ አስተማማኝ ኑሮ ከመኖራቸውም በላይ ለልጆቻቸው መልካም አርአያ ይሆናሉ።

ከዚህ ላይ መጠቀስ የሚገባው አንድ ቁም ነገር አለ እሱም ያለ ቁርባን በተክሊል ብቻ የሚፈጸመው የጋብቻ ሥነ ሥርዓት ነው፡ይህ ዓይነቱ፡የጋብቻ ሥነ ሥርዓት እንዲፈጸምላቸው የሚጠይቁ ወጣቶች ያልተገነዘቡት ነገር ያለ ይመስላል። ምክንያቱም በሥጋ ወደሙ /በቁርባን / ከታሠርኩ በኋላ ምናልባት ባትሆነኝስ /ባይሆነኝስ/ እንዴት ልፈታት እችላለሁ በሚል አስተሳሰብ ላይ ያተኩሩ በመሆናቸው ከቅዱስ ቁርባን ርቀው በተክሊል ብቻ ለመጋባት ማቀዳቸው ነው። ያም ሆነ ይህ በሞት ወይም በዝሙት ምክንያት ካልሆነ በቀር በማናቸውም መናኛ ምክንያት ሚስትን ወይም ባልን መፍታት በክርስትና ሕግ ፈጽሞ ያልተፈቀደ ስለሆነ በቁርባን ወይም በተክሊል ብቻ አግብቶ መፍታት ልዩነት እንደሌለው ቢያውቁ የዚህ ዓይነቱ ፍራቻ ሊወገድላቸው ይችላልና የቤተ ክርስቲያን አባቶችና መምህራን ወደ ጋብቻ ዓለም በማምራት ላይ የሚገኙትን ወጣቶች ከመጋባታቸው በፊት ስለ ሥርዓተ ጋብቻ በይበልጥ እንዲረዱ ስለክርስትና ሃይማኖትም ዕውቀት ይኖራቸው ዘንድ ለተወሰነ ጊዜ ኮርስ ቢሰጣቸው መልካም ነው ።

ምናልባት ባትሆነኝስ? ባንስማማስ የሚለው የጥርጣሬ መንፈስ አስቀድሞ መታሰብ የማይገባው ስለሆነ ክርስቲያኖች ይህን አይነት የጥርጣሬ መንፈስ ከሕሊናቸው አርቀው ዘላቂና አስተማማኝ የሆነውን ጋብቻ ለመመሥረት እንዲችሉ እግዚአብሔርን በጸሎት መጠየቅና አሳባቸውንም ሁሉ በእሱ ላይ መጣል አስፈላጊ ነው ። ከተጋቡም በኋላ «ባልና ሚስት አንድ አካል ናቸው» ተብሏልና አካሉን የሚጠላ እንደሌለ ሁሉ እርሰበርሳቸው በሰላምና በፍቅር መኖር አስፈላጊያቸው ነው።

ኢሳይያስ ወንድማገኘሁ

## ይህን ያውቁ ኖሮአል

ከገጽ ፲፬ የዞረ

ይህን የመሳሰሉ የሳይንስን ጥናትና ምርምር የሚጠይቁና የሚጠባበቁ አያሌ አስደናቂ ነገሮች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሞልተዋል ። ሐቀኛና በጐ ፈቃድ ያላቸውንም ጠበብትን ይፈልጋሉ።

በሚገኘውም ውጤት መጠን የመቅዱስ ትክክለኛነት እየተረጋገጠ ስለሚሄድ ስለ ሰው ልጆች ድኅነት የሚመሰክረው የቃሉ ዘር በመሬት ወድቆ ሳያፈራ እንደማይቀር እናምናለን ።

የዝናብ ነገር ከተነሳ ዘንዳ በቀድሞ ዘመን የነበሩ አሕዛብ ዝናም ከየት እንደሚመጣ እንዴትስ እንደሚዘንብ መነሻውን አያውቁም ነበር ። የሃይማኖት መጻሕፍቶቻቸውም ትክክለኛውን ነገር ሊያስረዱ አልተቻላቸውም እዚህ አንዱን ብቻ እጠቅሳለሁ ።

ያንዱ የሃይማኖት መጽሐፍ ፣ ዝናብ የሚጥለው ከጨረቃ ላይ መሆኑን ሲገልጽ መብረቅ ደግሞ ከጨረቃ እንዲያወዲያ ርቆ ከሚገኝ ሥፍራ ተልኰ እንደሚመጣ ነገር አድርጐ ይናገራል ።

— // —



# መልካም ዜና ለአብያተ ክርስቲያናት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት በየአብያተ ክርስቲያናቱ የደረሰውን የልብሰ ተክህኖ ችግር ለመቋቋምና ቀስ በቀስም ለማስወገድ እንዲሁም ካህናትና ምዕመናንም ቤተ ክርስቲያንን ለመርዳት ሲሉ አልባሳት ለመግዛት በሚጠይቁበት ጊዜ ደህና ሆኖ የተሠራ አልባሳት በተመጣጠነ ዋጋ ባለማግኘታቸው በተለይም በገጠር በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ላይ የልብሰ ተክህኖ ችግር መድረሱን በመገንዘብ መሥሪያ ቤታችን የአልባሳት ማደራጃ አቋቁሞ ሥራው በደህና ሁኔታ ሲከናወን ቆይቷል ።

አሁን ዝግጅቱ ደህና ውጤት እያሳየ በመሄዱ ሥራውን በበለጠ አዘጋጅቶ ፤ የጨርቁ ዓይነት ለአልባሳት እንዲያገለግል ተብሎ በተሠራው ጨርቅ ልብስ ተክህኖው ለረጅም ጊዜ አገልግሎት እንዲሰጥ ሆኖ እየተሰፋ ነው ።

ስለዚህ አብያተ ክርስቲያናትን ለመርዳት የምትፈልጉ ሁሉ በመሥሪያ ቤታችን ልብሰ ተክህኖውን አዘጋጅቶ ስለሚጠብቅ በመንበረ ፓትርያርኩ ጠቅላይ ጽ/ቤት ግቢ በመምጣት አልባሳቱን በተመጣጠነ ዋጋ ለመግዛት የምትችሉ መሆኑን እናሳስባለን ።

"ኢትዮጵያ ትቅደም"

የቤተ ክህነት ጠ/ጽ/ ቤት



በጠቅላይ ቤተ ክህነት እየተዘጋጀ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚቀርበው ልብሰ ተክህና



www.ethiopianorthodox.org

# ሊቃውንቶቻችን

## መምህር ወልደ ጊዮርጊስ ሀብተ ማርያም

(የሣር ብ/ጌታ ኅሩይ ወ/ሥላሴ የሐዲስ ኪዳን ትርጓሜ መምህር)

ስማቸው ከዚህ በላይ የተነገረው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ሊቅ የትውልድ ሀገራቸው በሸዋ ክፍለ ሀገር በተጉለትና ቡልጋ አውራጃ በሚጣቅ አማኑኤል አካባቢ ጽዋይ ቅዱስ ሚካኤል ከተባለ ቀበሌ ነው ።

የተወለዱትም መምሬ ሀብተማርያምና ወይዘሮ እኅተ ማርያም ከተባሉ ፡ በተክሊል በሥጋወደሙ ከተወሰኑ ሕጋውያን ባልና ሚስት በ1848 ዓ.ም. መሆኑ ተረጋግጧል ።

የእድሜ ገደባቸው ለትምህርት ሲደርስ ከሚጣቅ አማኑኤል መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ገብተው ዳዊት ከደገሙ፣በኋላ ግብረ ዲቁና አጥንተው ክህነታዊ አገልግሎታቸውን ሲፈጽሙ ከቆዩ በኋላ ወደ ጐንደር ሂደው ፀዋትወ ዜማ እንዲሁም ቅኔ በሚገባ አድርገው ተማሩ ።

የትምህርትና የምርምር ሑደታቸውን አቅጣጫ ለማስያዝ በነበራቸው አርቆ አመለካከት ከወልደ አብ ወልደ ሚካኤል ዘንድ ትርጓሜ ሐዲሳትን መልሰውና መላልሰው ለማስተማር በሚያስችል ሁኔታ አጥንተዋል የብሉያትንም ትርጓሜ ተከትለዋል በመሆኑም ብዙዎቹ ሊቃውንት በዘይቤ አፈታትና በትርጓሜ አወራረድ ችሎታቸው ብቻ ሳይሆን በምርምርና በአስተያየት ይዞታቸው በጣም ያደንቋቸዋል ።

በድንግልና በንጽሕና ፀንተው መኖራቸውም ከሊቅነት ጋር ፍጹም መንፈሳዊ ለመሆናቸው ማረጋገጫ ሆኗል ፤ይህም ዓይነቱ የብቻኝነት ኑሮ አሥራወ መጻሕፍትን ለማያያዝና ምሥጢራትን በየስልታዊ አቀራረባቸው ለመመርመር መልካም ዕድል ሰጥቷቸዋል ።

ትምህርታቸውን በጐንደር በሰፊው ካጠናቀቁና ሊቅ የሚያሰኛውን የመተርጐማን ሊቃውንት ስም ከወረሱ በኋላ ከመማር ወደ ማስተማር ዓለም ለመዛወር ባላቸው ዕቅድ መሠረት ወደትውልድ አገራቸው ተመልሰው በሚጣቅ ቅዱስ አማኑኤል አካባቢ ጉባኤያቸውን ዘርግተውና ደቀ መዛሙርቶችን ሰብስበው ያስተምሩ ጀመር የሊቁን የትምህርት ጥልቀት እንዲሁም የጉባኤ ስፋት የተረዱትና በዚያን ጊዜ አዲስ ቅኝ የነበረው የእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ደብር አስተዳደሪ የነበሩት ጸሐፌ ትዕዛዝ ገብረ ሥላሴ ደብዳቤ ልከው ከሚጣቅ አማኑኤል ወደ አዲስ አበባ እንዲመጡ አድርገዋል ።

ወዲያውም ለዓፄ ምኒልክ አቅርበውና አነጋገረው በቂ የሆነ መተዳደሪያቸውን በማሰጠት በእንጦጦ ራጉኤል ደብር ጉባኤ ዘርግተው እንዲያስተምሩ ሆኗል ፤ ይልቁንም ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ የሚኖሩበትንም ሆነ የሚያስተምሩበትን ቤት ራሳቸው ስለአሰሩላቸውና ለተማሪዎቻቸውም የሚያስፈልገውን ሁሉ ስለአዘጋጁላቸው ሊቁ ከልብስ ከምግብ ከመኖርያ ቤትና ከመሳሰለው ሁሉ ከዚህ ዓለም ችግር ተላቅቀው የማስተማርና የምርምር ተግባራቸውን አንድ ወገን ሆነው ቀጠሉ ዝናቸውም ከአንዱ ወደ ሌላው ስለአስተጋባና የጉባኤውን የሥራ ይዘት ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ በቅርብ እየተከታተሉ በማናቸውም ዓይነት ችግር ላይ ስለሚደርሱ ደቀ መዛሙርት በብዛት ተሰብስበውላቸው ጉባኤ ሰፋላቸው ።

ሊቁ የተጠየቁትን እንደተማሪዎቹ ፍላጐትና ጥያቄ ከማስተማር በቀር የትምህርት ዓይነት የማይመርጡና ይህንካልተማራችሁ ተመለሱ የማይሉ ስለነበሩ ከትርጓሜ መጻሕፍት ጋር ለሕፃናት ንባብ ለቀሳውስቱና ለዲያቆናቱ የሰዓታት ዜማ ያስተምሩዋቸው ነበር ።በመሆኑም በቅዱስ ራጉኤል ደብር ይደረግ የነበረው የሰዓታት ቁመት ከበሮና ጽናጽል ከሚጐድለው በቀር ካማኅሌት ሊተያይ ይችል እንደነበረ ይነገራል ።

የሊቁ የምግብ ሰዓት በአንድ ጊዜ የተወሰነ በመሆኑ አብዛኛዎቹ ሰዓታት ለጉባኤ ለጸሎትና ለምርምር ብቻ የተወሰኑ ነበሩ ።

በዚህ ሁኔታ ብዙዎችን ሊቃውንት በእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ደብር በትምህርት ከወለዱ በኋላ መልአከ ገነት ተድላ በኋላ ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ የገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስን ደብር በሚያስተዳደሩበት ወቅት ለንግሥት ዘውዲቱ ምኒልክ አሳስበው ከእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ወደ ገነተ ጽጌ መናገሻ ቅዱስ ጊዮርጊስ ተዛውረው እንዲያስተምሩ አድርገዋል ።

ሊቁ በመናገሻ ቅዱስ ጊዮርጊስ ደብር ጉባኤያቸውን አስፋፍተው በማስተማር ላይ እንዳሉ በ1917 ዓ.ም. ከመንግሥት አስፈቅደው በንባብና በትርጓሜ ብቻ ያወቁዋቸው የነበሩትን ቅዱሳት መካናት በቅድስት አገር በኢየሩሳሌም በዓይናቸው አይተውና እጅ ነሥተው ከቅዱሳን አበውም ቡራኬ ተቀብለው ተመልሰው ጉባኤያቸውን ቀጥለዋል

ምንም ቢሆን በዕድሜ ከቆዩ ዘንድ መድከምና ማርጀት አይቀርምና መምህር ወልደ ጊዮርጊስ ሀብተ ማርያም በመማርና በማስተማር ለረጅም ጊዜ ከኖሩ በኋላ የርጅና ድካም ይታይባቸው ጀመር ።

በዚህም ጊዜ ከደቀመዛሙርቶቻቸው አንዱ የነበሩት ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ሰውነትዎ ስለደከመ ማስተማሩን ይተውትና ዕረፍት ያድርጉ ቢሏቸው “ አልክ አልክና ደግሞ አታስተምር ትለኝ ጀመር እኔኮ የሞት ጥላ እስኪጋርደኝና የመቃብር አፈር ሰውነቴን እንዳልነበረ እስኪያደርገው ድረስ ጉባኤ አይታጠፍም ይልቁንስ ቀብሬ በደብረ ሊባኖስ ገዳም እንዲፈጸም እፈልጋለሁና ሬሣዬ በሰው ትከሻ ከሚጓዝ አሁን በሕይወት ሳለሁ እኔው በእግሬ ሄጄ ሥጋዬ ከዚያው እንዲያርፍ አደርጋለሁ ብለው መልስ ሰጡዋቸው ።

ብላቴን ጌታ ኅሩይም እኛ ልጆችዎ እያለን ለምን ያስባሉ ? የእግዚአብሔር ፈቃድ ይጨመርበት እንጂ ምንም ቢሆን ለደብረ ሊባኖስ አፈር ሳናበቃዎ አንቀርም ፣ አሁን ግን ተማሪዎችዎ እንዳይጉላሉ እርስዎም በበለጠ ድካም እንዳይሰማዎ አርፈው ይቀመጡ ብለው እያጽናኑ በሰፊው መከሯቸውና ለጊዜው ከዚያው ካሉበት እንዲቆዩ ሆነ ።

ይሁን እንጂ የሰውና የእግዚአብሔር ሃሳብ የተራቀቀ በመሆኑ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ በእንግሊዝ አገር ከርሳቸው ቀድመው መስከረም 9 ቀን 1931 ዓ.ም. በሞት መለየታቸውን ስለሰሙ ጽኑዕ የሆነ ኃዘን ተሰማቸው ።

ወዲያው ወደደብረ ሊባኖስ ገዳም ሔደው የትርጓሜ መጻሕፍት ጉባኤያቸውን ሲቀጥሉ ከቆዩ በኋላ መዓርገ ምንኩስና ተቀብለውና የኢትዮጵያን የነፃነት ትንሣኤ አይተው መስከረም 29 ቀን 1939 ዓ.ም. በተወለዱ በ91 ዓመት ዕድሜያቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ ።


አለቃ ዓምደ ጽዮን ተሰማ

## ቅዱስ ፓትርያርኩ . . . . . .

ከገጽ ፱ የዞረ

ድተው ንግግራቸውን አጠቃለዋል ።

ከመምህር ብርሃነ ሥላሴ ንግግር ቀደሳን ንሕነ”የሚለውን ያሬዳዊ መዝሙር ለአምስት ደቂቃ ያህል አሸብሸቀባበል ሥነ ሥርዓት በዚህ ሁኔታ እንደተፈጸመ ቅዱስነታቸው ከብፁዓን ጳጳሳቱና ከቤተ ክህነት ባለሥልጣኖች ጋር በመሆን ቤተ መድኃኔዐለምን ጐበ



የላሊበላ ወጣት መዘምራን

ም ሲል የላሊበላ መንፈሳውያን ወጣቶች “ኢኮነንግደ ወፈላሲ ሀገሪቶሙ ለቅዱበዋል ።


በአውደ ምህረቱ ላይ የተደረገው የአኙ ቤተ መድኃኔዐለም ቅዱስ ላሊበላ ካነፃቸው አሥር ቤተ መቅደሶች አንዱ



www.ethiopianorthodox.org

ሲሆን በውስጥ አስራ ስምንት በውጭ 34 በጣራው ላይ 20 አእማድ ምሶሶች ያሉት እጅግ በጣም ትልቅና አስደናቂ መለከቱና ሥርዓተ ቅዳሴው ከተከናወነ በኋላ ለቅዱስነታቸው ወደ ተዘጋጀው የማረፊያ ቦታ ዓምርተው ለጥቂት

3- ብፁዕ ዶክተር አቡነ ገብርኤል በሀረርጌ ክፍለ ሀገር የሰሜንና የምዕራብ አውራጃዎች ጳጳስ



ሰባ ሁለት አዕማድ (ምሰሶዎች) ያሉትና እጅግ አስደናቂ የሆነው ሕንፃ ላሊበላ (ቤተ መድኃኔ ዓለም) ይህ ነው

የሆነ ግሩም ሕንፃ ነው ። አምዶቹ ምሶሶዎቹ ሲደመሩ ሰባ ሁለት 72 ይሆናሉ ። በሰባ ሁለቱ አርድእት ምሳሌ የተሰሩ መሆኑን ያመለክታል። ከዚያም ጉብኙቱ ወደ ቤተ ማርያም ቀጠለ ቤተ ማርያም በውስጥ ስድስት በውጭ ስድስት አእማድ ያሉት አስደናቂ ሕንፃ ነው ። አምዶቹ (ምሶሶዎቹ በአንድ ላይ አሥራ ሁለት ሲሆኑ የአስራ ሁለቱ ሐዋርያት ምሳሌዎች ናቸው ። ቤተ ማርያም በየአመቱ የልደት በዓል የሚከበርበት በመሆኑ በዕለቱ የልደት ዋዜማ ሥነ ሥርዓት ይደረስበት ነበር ። ቅዱስነታቸውም በዚያው ተገኝተው የዋዜማውን ሥነ ሥርዓት ከተ

ጊዜ ዕረፍት ካደረጉ በኋላ ከቀኑ በ11 ሰዓት ላይ በላሊበላ አዲስ የተመሠረተውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የድሆች ሕፃናት ማሳደጊያ ድርጅት መርቀው ከፍተዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ እና የቅዱስ ሲኖዶስ ሊቀ መንበር የሕፃናቱን ማሳደጊያ ድርጅት መርቀው በከፈቱበት ሥነ ሥርዓት ላይ ፣

1- ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል የወሎ ሃገረ ስብከት ጳጳስ

2- ብፁዕ አቡነ ኤፍሬም የአርሲ ሃገረ ስብከት ጳጳስ

4- አቶ መርስኤ ሃዘን አበበ የጠ ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ

5- መምህር ገ/እግዚአብሔር ሀጋዬ የፓትርያርኩ ልዩ ፀሐፊ

6- ሊቀ ሀሩያን መርሐ ዕድቅ ገ/ሕይወት የሸዋ ሃ/ስብከት ሥራ አስኪያጅ

7- መጋቢ ካህናት ብርሃኑ መኩንን የመንፈሳዊ አገልግሎት መምሪያ ኃላፊ

8- ጓድ የመቶ አለቃ ጌታቸው ተቀባ የላስታ አውራጃ አስተዳዳሪ

9- ዶክተር ሽፈርድ በኢትዮጵያ የጀርመን ቤተ ክርስቲያን ካህን



10- አቶ ፀጋዬ በርሔ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የህፃናት አስተዳደግ ጉባኤ ጸሐፊና ሌሎችም ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የሕፃናትን ማሳደጊያ ድርጅት መርቀው ከከፈቱ በኋላ በሥነ ሥርዓቱ ላይ ለተገኙት እንግዶች መንፈሳዊና አባታዊ ንግግር አድርገዋል ።

ቅዱስነታቸው ባደረጉት ንግግር"በዚህ በተቀደሰ ቦታ ተገኝተን የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ በዓለ ልደት ስናከብር ይህንን የሕፃናት ማሳደጊያ ድርጅት መርቀን በመክፈታችን ለእግዚአብሔር ምስጋና እናቀርባለን" ብለዋል ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ንግግራቸውን በማራዘም "ሕንጻ ሥላሴና ሕንፃ ሰብእ አሉ ሕንፃ ሥላሴ የሰው ልጅ ሲሆን ሕንፃ ሰብእ ግን አሁን እንደምናየው በሚያስገርምና በሚያስደንቅ ሁኔታ በሰው እጅ የታነፁትና አምልኮታችንን የምንፈፅምባቸው የአብያተ ክርስቲያናት ሕንፃዎች ናቸው ። ሁሉንም መንከባከብ አስፈላጊ ቢሆንም ለሰው ልጆች የሚደረገው እንክብካቤ ከሁሉም የላቀና ቅድሚያ የሚሰጠው ነው" ካሉ በኋላ እስከ አሁን ድረስ ለሕፃናት ይደረግ የነበረው እንክብካቤ አጥጋቢ እንዳልነበረ ገልፀው አሁን ግን በመንግሥትም ሆነ በቤተ ክርስቲያን በኩል አሳዳጊና ረዳት ለሌላቸው ሕፃናት የሚደረገው ጥንቃቄ ከፍተኛ መሆኑን አስረድተዋል። ቅዱስነታቸው ንግግራቸውን በመቀጠል ሕፃናት በእንክብካቤ ቢያድጉ ሀገር ወዳድ ዜጎች እንደሚሆኑ አስገንዝበው ሕፃናትን ተንከባክቦ በማሳደግ ረገድ ቤተ ክርስቲያንም ከፍተኛ ድርሻ ያላት ሲሆን ይህንም ድርሻዋን በመፈፀም ላይ የምትገኝ መሆኑን በንግግራቸው ገልጠዋል ።

ከዚህ ቀደም ሲል አቶ መርስኤ ሃዘን አበበ የጠ/ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅና የሕፃናት አስተዳደግ ጉባኤ ሊቀ መንበር ቅዱስ ፓትርያርኩ የህፃናት ማሳደጊያውን ድርጅት መርቀው መክፈታቸውን አስመልክተው ንግግር አድርገዋል ። ሥራ አስኪያጁ ባደረጉት ንግግር ላሊበላ የቀረው የታሪክ ቦታዎች ብቻ እንጅ ንዋያተ ቅድሳቱና ቅርሳ ቅርሱ ግን ተሠርቀው ያለቁ መሆናቸውን ገልፀዋል።አቶ መርስኤ ንግግራቸውን በመቀጠል ይህ ታሪካዊ ቦታ ባለፉት መንፈሳውያን አባቶች(ፓትርያርኮች) ያልተጐበኘና እንደ አልባሌ ተዘንግቶ የኖረ መሆኑን አመልክተው ይህ ታሪካዊ ቦታ በአንድ ፓትርያርክ ሲጐበኝ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የመጀመሪያ ፓትርያርክ መሆናቸውን አስረድተዋል ።

አቶ መርስኤ ለላሊበላ ካህናት መረጃ ይሆን ዘንድ የጐጀ እንዱስትሪ በቅርቡ እንደሚቋቋመው በቅዱስነታቸው የተሠጠውን ተስፋ አስታውሰው ይህም ሳይዘገይ እንደሚፈፀምና ካህናቱ በሚቋቋመው የጐጀ እንዱስትሪ እየሠሩ ይህን የተቀደሰ ቦታ ለማገልገል እንደሚችሉ ያላቸውን እምነት ገልጠዋል ።

ከሥራ አስኪያጁ ንግግር ቀደም ሲል በኢትዮጵያ የምዕራብ ጀርመን ቤተ ክርስቲያን ካህን ዶክተር ሽፈርድ በአደረጉት ንግግር በጀርመን ቤተ ክርስቲያን አባላትና በጀርመን ክርስቲያን ተራድዖ ድርጅት ስም ለቅዱስ ፓትርያርኩና ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን አባላት ሰላምታ ካቀረቡ በኋላ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ረዳት የሌላቸውን ሕፃናት በማሳደግ ለምታደርገው አስተዋጽኦ የምዕራብ ጀርመን ክርስቲያናዊ ድርጅት ርዳታ የማይለያት መሆኑን ገልጠዋል ።

ዶክተር ስለ ዕለቱ በዓል ሲናገሩ በአውሮጳ በዓለ ጥምቀት በኢትዮጵያ በዓለ ልደት የሚከበርበት የክርስቲያኖች ዳግም ልደት መሆኑን አሳስበው ወደ ታሪክ መለስ በማለት "ንጉሥ ላሊበላ ለትውልድ አኩሪ የሚሆኑ እነዚህን አሥር አብያተ መቅደስ እንደሚያነፅና ታላቅ የሕዝብ መሪ እንደሚሆን በተወለደበት ዕለት እንደተመረጠ ታሪክ ያስታውሰናል ፣ ዛሬ እኛን የሚመርጡን እንደርሱ አብያተ መቅደስን ለማነፅ ብቻ ሳይሆን አሳዳጊ የሌላቸውን ሕፃናት በምግብና በትምህርት አንፀን እንድናሳድጋቸው ነው" ብለዋል ።

ከዚህ ቀደም ሲል አቶ ፀጋየ በርሄ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የሕፃናት አስተዳደግ ጉባዔ ጸሐፊ ባደረጉት ንግግር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዘጠኝ ክፍላተ ሀገር የሕፃናት ማሳደጊያ ድርጅቶችን አደራጅታ አራት ሺህ አንድ መቶ ሰባ 4.170 አሳዳጊና ረዳት የሌላቸውን ሕፃናት እንደምትረዳ ገልጠዋል ። በዕለቱ ተመርቆ የተከፈተውም የላሊበላ የሕፃናት ማሳደጊያ ድርጅት ለጊዜው ሰባ 70 ሕፃናትን የተቀበለ ሲሆን ወደፊት ግን የሕፃናቱ ቁጥር ወደ መቶ 100 ከፍ እንደሚል አስረድተዋል ።

በበዓሉ ላይ ለተገኙት እንግዶች የሻይ ግብዣ ተደርጐ በቅዱስ ፓትርያርኩ ቃለ ቡራኬ የበዓሉ ሥርዓት ተፈጽሞአል ።

ማክሰኞ ለረቡዕ አጥቢያ በ29 4 73 ዓ.ም. ከሌሊቱ በ9 ሰዓት ፓትርያርኩ ከብፁዓን ጳጳሳት ጋር በመሆን በቤተ ማርያም ተገኝተው ስለ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዓለ ልደት የሚደረሰውን ስብሐተ ማኅሌት ተመልከቱ ።

የጸሎት ቅዳሴው ሰዓት ሊደርስ ጸሎተ ቅዳሴው በብፁዕ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ መሪነት በብፁዓን ጳጳሳት ተራዳኢነት ተከናወነ ።

ፀሎተ ቅዳሴውም ተከናውኖ እንዳበቃ ሥራተ ዑደት በአንድ ሰዓት ተጀመረ ሥርዓተ ዑደቱ ከመጀመሩ በፊት ሥርዓተ ዑደቱን ለመመልከት አመች በሆነ በማሜ ጋራ ላይ ለቅዱስነታቸውና ለተከታዮቻቸው በተዘጋጀው የክብር ሥፍራ ቅዱስነታቸው ከብፁዓን ጳጳሳት ጋር በመሆን ሥርዓተ ዑደቱን



www.ethiopianorthodox.org

ተመልክተዋል ።

በላሊበላ የሚደረገው ሥርዓተ ዑደት በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ከሚደረገው ዑደተ ታቦት የተለየ ነው ። ይኸውም በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት የሚደረገው ዑደተ ታቦት ዕላት ተሸክሞ በመውጣትና ቤተክርስቲያኑንበመዞር ሲሆን በላሊበላ የሚደረገው ሥርዓተ ዑደት ግን በሥዕል አድህኖና በመስቀል ብቻ ነው ። ከዚህም ሌላ የላሊበላው ሥርዓተ ዑደት መላእክት ከኖሎትኖሎት ከመላእክት ጋር አንድ ሁነው በዕለተ ልደት ያመሰገኑትን ስብሐተ ማህሌ በውዝ ዋዜ ሲዘምሩ ከታች በመቅደሱ ዙሪያ ያሉት ካህናት "ቤዛ ኩሉ ዓለም ዮም ተወልደ" እያሉ በመቀባበል ሲዘምሩ በሕንፃው አፋፍ ላይ ያሉት መላእክትን ከታች በመቅደስ ዙሪያ ያሉትኖሎትን መስለው ስለሚታዩ ነው። ሥርዓተ ዑደቱ በዚህ ሁኔታ ከተፈጸመ በኋላ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በዓሉን ለማክበር ለተሰበሰቡት መዕመናን ቃለ ምዕዳን አሰምተዋል ። ቅዱስነታቸው ባሰሙት ቃለ ምዕዳን "አዳምና ሔዋን ስለበደሉ አምላካችን እኛን ስለወደደ በእኛ በሀርይ ሰው ሁኖ ችሁ እዕፍ ድርብ ነው በማለት ካስረዱ በኋላ በቅዱስነታቸው ቃለ ቡራኬ የበዓሉ ፍጻሜ ሆኖአል ።

ከዚህ ቀደም ሲል ግን ብፁዕ አቡነ ገብርኤል

"እነሆ በዳዊት ከተማ መድህን ክርስቶስ ተወልዶላችኋል" በሚል ርዕስ ተነስተው ሰፋ ያለ ትምህርት ሰጥተዋል ። ብፁዕነታቸው ይህ የምሥራች የተነገረው በሰማያውያን መላእክት አንደበት መሆኑን ገልጠው የክርስቶስ ልደት ሰዎችና መላእክት አንድ ሆነው ያመሠገኑበት ሰዎች ከእግዚአብሔር



የላሊበላ ሥርዓተ ዑደት በማሜ ጋራ ላይ

ት የሚያስታውስ ነው ። ምክንያቱም ጥንግ ድረስ የለበሱ ካህናት በአንድ በኩል ሸማ የለበሱት በሁለተኛው ገጽ እንዲሁም ካባ የለበሱት በሦስተኛው ረድፍ ሆነው ከህንፃው አፋፍ ላይ (ማሜ ጋራ)በመቆም" ቤዛ ኩሉ ዓለም ዮምተወልድ " እያሉ በስግደትና ተወለደ ። ዓለሙ በሙሉ የእርሱ ሲሆን እኛን ሰዎችን ለማዳን ስለእኛ ተዋረደ ። የእርሱ ውርደት ለእኛ ክብር ሆነ ። እናንተም ይህን የተደረገላችሁን ሁኔታ አስባችሁ በዚህ የቃልኪዳን ቦታ የመድኃኒታችን የኢየሱስክርስቶስን በዓለ ልደት ለማክበር ስለመጣችሁ ዋጋ ጋር የታረቁበት የሰዎች ሰላምና ነፃነት የተገኘበት መንፈሳዊ በዓል መሆኑን አስረድተዋል ።


ከዚህ በኋላ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ብፁአን ጳጳሳትን አስከትለው 1ኛ ቤተመስቀልን 2ኛ ቤተ ደናግልን 3ኛ ቤተ ጐልጐታ ሚካኤልን 4ኛ



ቤተጊዮርጊስን 5ኛ ቤተ ሊባኖስን ጐበኙ ከቀኑ ስምንት ሰዓት ሲሆን ደግሞ ቤተ አማኑኤልን ቤተ ገብርኤልንና ቤተ መርቆሬዎስን ጐብተዋል ።

በነገራችን ላይ ቅዱስ ላሊበላ ያነፃቸው አብያተ ክርስቲያናት አሥር ሲሆኑ እነርሱም

1ኛ ቤተ ማርያም
2ኛ ቤተ መድኃኔዐለም
3ኛ ቤተ መሥቀል
4ኛ ቤተ ደናግል
5ኛ ቤተ ጐልጐታ ሚካኤል
6ኛ ቤተ ገብርኤል
7ኛ ቤተ ሊባኖስ
8ኛ ቤተ መርቆሬዎስ
9ኛ ቤተ አማኑኤል
10ኛ ቤተ ጊዮርጊስ ሲሆኑ አሁን በስራ ላይ የሚገኙት ዘጠኙ ብቻ ናቸው ቤተ መርቆሬዎስ የተባለው ሕንፃ ግን ጠጋኝ ባለማግኘቱ ምክንያት ይመስላል ሕንፃው ተሰነጣጥቆ ከአገልግሎት ውጭ ሆኖአል ። ሌሎችም ሁሉ ከፍተኛ ጥንቃቄ ካልተደረገላቸው እንዲሁ



ካህናቱ በማሜ ጋራ ላይና ታች በቤተ ማርያም «ቤዛ ኵሉ ዓለም ዮም ተወለደ» እያሉ በመቀባበል ሲዘምሩና ሥርዓተ ዑደት ሲያደርሱ

ከጥቅም ውጭ እንዳይሆኑ ያሰጋል የጉብኝቱ ፕሮግራም በዚህ ሁኔታ ከተፈጸመ በኋላ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ብፁአን ጳጳሳትን አስከትለው በመጡበት አኳኋን ወደ አዲስ አበባ ተመልሰዋል ። ቅዱስነታቸው ወደ አዲስ አበባ ሲመለሱ

1ኛ ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል የወሎ ሃገረ ስብከት ጳጳስ
2ኛ አቶ መርስኤ ሃዘን አበበ የጠቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ
3ኛ መምህር ገብረ እግዚአብሔር ፀጋዬ የፓትርያርኩ ልዩ ጸሐፊ
4ኛ መጋቢ ካህናት ብርሃኑ መኰንን የመንፈሳዊ አገልግሎት መምሪያ ሐላፊ (በሹምሻሃ) ኤሮፕላን ማረፊያ ተገኝተው አሸኛኘት አድርገውላቸዋል ።

——— // ———



www.ethiopianorthodox.org

# የመጽሐፍ ቅዱስ ጥያቄዎች ውድድር መልስ፡-

አቅርበንላችኋል ።
በኅዳር 1973 ዓ.ም ላወጣናቸው ጥያቄዎች መልስ ከዚህ እንደሚከተለው አቅርበንላችኋል ።
በኅዳር 1973 ዓ.ም ላወጣናቸው ጥያቄዎች መልስ ከዚህ እንደሚከተለው ሊወጡ በዝግጅ

1. እስራኤላውያን እርሾ ያልገባበት ቂጣ እንዲበሉ የታዘዙት ከምድረ ግብፅ አርነት ሊወጡ በዝግጅ ት ላይ ሳሉ እግዚአብሔር በሙሴ ባዘዛቸው መሠረት ሲሆን ለሰባት ቀናት በየዓመቱ እንዲያከብ ሩት ታዘው ነበር ። በመንፈሳዊ ትርጉም ከአሮጌው ሰው ፤ ከአሮጌው ኑሮ ፤ መላቀቅ ነው ። ታሪኩ በዘጸአት መጽሐፍ ምዕ. 12 ይገናኛል ።
2. ክርስቲያን የምድር ጨው መባሉ፡- ጣዕም ለሌለበት ዓለም ጣዕም ሰጪነቱንና ከመበስበስ ጠባቂ ነቱ ይጠቁማል ።
3. የመላእክት ቁጥር ስንት እንደሆነ በትክክል ማወቅ ባይቻልም መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- "የእግዚአብሔር ሠረገላዎች የብዙ ብዙ ሺህ ናቸው ።" መዝ.68፡17 ራእ ፡ 5 ፡ 11
4. እግዚአብሔር ሲጠራው ድምጹን መለየት የተሳነው ወጣት፡-ሳሙኤል ነበረ ። 1ኛሳሙ.3
5. እስራኤል ከምድረ ግብፅ ነፃ ከወጡ በኋላ ናፈቁን ያሏቸው ምግቦች በግብፅ ሳሉ ይመግቧቸው የነ በሩትን ነው ዘኁ.16፡ዘፍ.11፡5
6. ኢትዮጵያዊቱ የሙሴ ሚስት ስሟ ማን እንደነበረ አልተጠቀሰም ። ዘፍ. 12 ፡ 1
7. በብሉይ ኪዳን በሩዋጪነቱ ታዋቂ የነበረው ወጣት አሣኤል ነበረ ። 2ሳሙ.2፡18
በጉደለው ቦታ የተሞሉ ቃላት ፡
8. አምላክህን ለመገናኘት ተዘጋጅ ። አሞጽ.4፡12
9. እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ እኔም አሳርፋችኋለሁ ። ማቴ.11፡38
10. እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ ፤ ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ ወደ እርሱ እገባለ ሁ ። ራዕ.3፡20 ።

በዚህ ውድድር አሸናፊዎች ፡
1. አቶ ዓለማዬሁ ጉልላት
2. ወ/ሮ እራጋው መኩሪያ
3. አባ ገ/ሥላሴ ኃይሉ ናቸው ።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር

የመ.ሣ.ቁጥር 1252
አዲስ አበባ



# ኢ.ኦ.ተ.ሐ.ድ

ማሳሰብያ ለምእመናን በሙሉ

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፤ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፣ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፤ ትምህርቶችንና የል ማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅ ርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀ ረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመ ረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት

ስልክ ቍ. 116616
የመል. ሣ. ቍ. 3137
አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org